አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረምረቃ መርሃግብር

# የቃላት ትምህርት አተገባበር ትንተና

## (በጉራጌ ዞን በቡታጅራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪነት)

በ አሸናፊ ንጋቱ

መስከረም ፣ 2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ

# የቃላት ትምህርት  አተገባበር ትንተና

## (በጉራጌ ዞን፣ በቡታጅራ ከተማ፣ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የዘጠነኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪነት)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድኅረምረቃ መርሃግብር

ለአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል አማርኛን ለማስተማር

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተዘጋጀ ጥናታዊ ጽሑፍ


አማካሪ

ዳዊት ፍሬሕይወት (ዶ/ር)



መስከረም ፣ 2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ኮሌጅ

# የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

# የድኅረምረቃ መርሃግብር

ይህ "የቃላት ትምህርት አተገባበር ትንተና (በጉራጌ ዞን፣ በቡታጅራ ከተማ፣ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የዘጠነኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪነት)" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በአሸናፊ ንጋቱ የቀረበ ጥናት፣ የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና ወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ቀርቧል፡፡

**የፈታኝ ቦርድ አባላት**

አማካሪ ------------------------------------------ ፊርማ ----------------- ቀን -------------

የውጭ ፈታኝ ------------------------------------ ፊርማ ----------------- ቀን --------------

የውስጥ ፈታኝ ------------------------------------ ፊርማ ---------------- ቀን ---------------

# ምስጋና

በቅድሚያ አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠል ጥናቱን እንዴት ማካሄድ እንዳለብኝ አቅጣጫ በማመልከት፣ በማረምና በማስተካከል ታላቅ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለአማካሪዬ ዳዊት ፍሬሕይወት (ዶ/ር) ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በተጨማሪ ጥናቱን ለማካሄድ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም ጥናቱን ሳካሄድ ተገቢውን ትብብር ላደረጉልኝ ለቡታጀራ ከተማ በህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራንና መምህራን እንዲሁም ለተማሪዎች ላቅያ ለምስጋና አቀርባለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የቃላት ትምህርት አተገባበር በተመለከተ በጉራጌ ዞን በቡታጀራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪነት የተከናወነ ጥናታዊ ስራ ነው፡፡ ጥናቱ  ዓይነታዊ ምርምር እና አሃዛዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን በቡታጅራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል መምህራን የቃላት ትምህርት አተገባበር በተጨማሪ የቃላት ትምህርት አቀራረብ እና በቃላት ትምህርት የተማሪዎች ተሳትፎ በመፈተሽ ትንትና ተደርጓል፡፡ በዚህ ጥናት የተካተቱ መምህራን ቃላትን እንዴት እንደሚያቀርቡ፤ በመማር ማስተማር ሂደት ቃላትን እንዴት እንደሚተገብሩ እና ተማሪዎች ቃላትን በመማር ሂደት ያላቸውን ተሳትፎ ለመመልከት መረጃዎችን ከመምህራን እና ከተማሪዎች እንዲሰበሰቡ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት የክፍል ውስጥ ምልከታ እና የጽሑፍ መጠይቆች በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተገኘ መረጃ መሰረት የቃላት ማስተማሪያ መንገዶች መካከል ቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍቻቸው ማቅረብ፤ ቃላትን በአውድ ማቅረብ እና ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ከማቅረብ አንፃር መምህራን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚተገብሯቸው፤ በአንጻሩም የቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ፣ ቃላትን አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ እና ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚጠቀሙባቸው ጥናቱ አመላክቷል። የመማሪያ መጽሐፍ እጥረት፣ የተማሪ መብዛት፣ የክፍለጊዜ መደራረብ፣ የቃላት ትምህርት የማስተማሪያ መንገዶችን አለመተግበር፣ ቃላትን የማስተማሪያ መርሖችን ያለመከተል፣ መረበሽ፣ የተማሪዎች ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆኑ እና ለቋንቋው የተሰጠው ክፍለጊዜ ማነስ የመሳሰሉ ችግሮች ለቃላት ትምህርት አተገባበር ተግዳሮት መሆናቸው ጥናቱ አመላክቷል።

# የይዘት ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ....... i
አጠቃሎ ....... ii
የይዘት ማውጫ ....... iii
የሠንጠረዥ ማውጫ ....... vi
ምዕራፍ አንድ ....... 1
መግቢያ ....... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ....... 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....... 3
1.3 የጥናቱ አላማ ....... 3
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ....... 3
1.5 የጥናቱ ወሰን ....... 4
1.6 የጥናቱ ውስንነት ....... 4
1.7 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ብያኔ ....... 4
ምዕራፍ ሁለት ....... 5
ክለሳ ድርሳናት ....... 5
2.1 የቃላት ምንነት ....... 5
2.2 ቃላትን የማስተማርና አስፈላጊነት ....... 6
2.3 የቃላት ትምህርት ማስተማሪያ መርሖች እና ማቅረቢያ መንገዶች ....... 9
2.3.1 የቃላት ትምህርት ማስተማሪያ መርሖች ....... 9
2.3.2 የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች ....... 11
2.3.2.1 በአውድ ማቅረብ ....... 12
2.3.2.2 ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት ማቅረብ ....... 15
2.3.2.2.1 ቃላትን በተመሳሳይ እና በተቃራኒ ፍች ማቅረብ ....... 16
2.3.2.2.2 የቃላት አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ ....... 16
2.3.2.2.3 የቃላት አብሮ ተሰላፊነት ....... 17
2.3.2.3 ቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ማቅረብ ....... 18
2.3.2.4 የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ....... 19

2.3.2.5 ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ.....19
2.3.2.6 ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ማቅረብ.....20
2.3.2.7 የቃላት ትምህርቱን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ.....20
2.3.2.8 ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ.....21
2.4 የመማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያዎች ለቃላት ትምህርት አተገባበር ያላቸው ሚና.....21
2.5 በቃላት ትምህርት አቀራረብ ና አተገባበር ላይ የሚያጋጥሙ ተለዋዋጮች.....23
2.6 የተዛማጅ ፅሑፍ ቅኝት.....23
ምዕራፍ ሶስት.....26
የጥናቱ ንድፍ እና መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች.....26
3.1 የጥናቱ ንድፍ.....26
3.2 የመረጃ ምንጮች.....26
3.3 የናሙና አመራረጥ.....26
3.3.1 የጥናቱ ክልል ናሙና አመራረጥ.....26
3.3.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ.....27
3.3.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ.....27
3.3.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ.....27
3.3.5 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ.....28
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች.....29
3.4.1 ምልከታ.....29
3.4.2 የፅሑፍ መጠይቅ.....30
3.5. የመረጃ አተናተን.....30
ምዕራፍ አራት.....32
የውጤት ትንተናና ማብራሪያ.....32
4.1 የመረጃዎች ውጤት ትንተና.....32
4.2 የቃላት ትምህርት ማስተማሪያ መርሖች በተመለከተ.....33
4.3 የቃላት ትምህርት ማስተማሪያ መንገዶች በተመለከተ.....34
4.3.1 ቃላትን በአውድ ማስተማር.....34
4.3.2 ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት ማቅረብ.....36
4.3.3 የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ቃላትን ማቅረብ.....39

4.3.4 የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ........................................41
4.3.6 ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ማቅረብ ..................................................................43
4.3.7 ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላትን ማስተማር ............................................45
4.3.8 ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ........................46
4.4 በቃላት ትምህርት የተማሪዎች ተሳትፎ በተመለከተ .................................................47
4.5 በቃላት ትምህርት አተገባበር ላይ የሚያጋጥሙ ተለዋዋጮች ................................48
4.6 የጥናቱ የውጤት ማብራሪያ ..................................................................................49
ምዕራፍ አምስት ........................................................................................................53
ማጠቃለያ እና አስተያየት .........................................................................................53
5.1 ማጠቃለያ..........................................................................................................53
5.2 መደምደሚያ.......................................................................................................54
5.3 አስተያየት .........................................................................................................55
ዋቢ መጻህፍት ..........................................................................................................57
አባሪዎች ..................................................................................................................60
አባሪ 1፡- ለዘጠነኛ ክፍል መምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ..............................................60
አባሪ 2 :- ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ...........................................63
አባሪ 3:- የቃላት ትምህርት ክንውን መከታተያ ቅፅ...........................................................66

## የሠንጠረዥ ማውጫ

**የአባሪ ርእሶች** **ገጽ**


ሠንጠረዥ 1፡- በመረጃ ሰጭነት የተሳተፉ መምህራን ዝርዝር መረጃ ..................................28

ሠንጠረዥ 2፡ የቃላት ትምህርት ማስተማሪያ መርሖች በተመለከተ ...................................33

ሠንጠረዥ 3፡ ቃላትን በአውድ ከማስተማር አንፃር በተደረገ ምልከታ የተገኘ መረጃ .............34

ሠንጠረዥ 4፡ ቃላትን በአውድ ከማስተማር አንፃር ለመምህራን ለቀረበ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ..35

ሠንጠረዥ 5፡ ቃላትን በአውድ ከማስተማር አንፃር ለተማሪዎች በቀረበ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ..35

ሠንጠረዥ 6፡ ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት ከማቅረብ አንፃር በተደረገ ምልከታ.....36

ሠንጠረዥ 7፡ ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት ከማቅረብ አንፃር የመምህራን ምላሽ ...37

ሠንጠረዥ 8፡ ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት ከማቅረብ አንፃር የተማሪዎች ምላሽ ...38

ሠንጠረዥ 9፡ የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት በምልከታ የተገኘ መረጃ.........39

ሠንጠረዥ 10፡ የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት የመምህራን ምላሽ...............39

ሠንጠረዥ 11፡ የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት የተማሪዎች ምላሽ...............40

ሠንጠረዥ 12፡ የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ በተመለከተ በምልከታ የተገኘ መረጃ.........................................................................................................41

ሠንጠረዥ 13፡ የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ የመምህራን ምላሽ ..................41

ሠንጠረዥ 14፡ የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ የተማሪዎች ምላሽ ..................41

ሠንጠረዥ 15፡ ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ በተመለከተ በምልከታ የተገኘ መረጃ .........................................................................................................42

ሠንጠረዥ 16፡ ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ በተመለከተ የመምህራን ምላሽ ...42

ሠንጠረዥ 17፡ ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ ...43

ሠንጠረዥ 18፡ ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ በምልከታ የተገኘ መረጃ....................43

ሠንጠረዥ 19፡ ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር የመምህራን በቀረበ ምላሽ .......44

ሠንጠረዥ 20፡ ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር የተማሪዎች ምላሽ .................44

ሠንጠረዥ 21፡ ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላትን ማስተማር በምልከታ የተገኘ መረጃ..45

ሠንጠረዥ 22፡ ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላትን ማስተማር በተመለከተ የመምህራን ምላሽ ..........................................................................................................45

ሠንጠረዥ 23፡ ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላትን ማስተማር በተመለከተ ለተማሪዎች ምላሽ ..........................................................................................................45

ሠንጠረዥ 24፡ ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል በምልከታ የተገኘ መረጃ...46

ሠንጠረዥ 25፡ ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት የመምህራን ምላሽ .46

ሠንጠረዥ 26፡ ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት የተማሪዎች ምላሽ .47

ሠንጠረዥ 27፡ በቃላት ትምህርት መምህሩ ተማሪዎችን ማሳተፉ በተመለከተ ምልከታ የተገኘ መረጃ..........................................................................................................47

ሠንጠረዥ 28፡ በቃላት ትምህርት የተማሪዎች ተሳትፎ በተመለከተ  ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ...48

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

McCarthy (1990)እና Taylor(1990) እንደሚገልጹት የቋንቋ ትምህርት አላማ የቋንቋ ክሂሎችን ማደራጀት፣ የሥነልሳንና የሥነፅሁፍ እውቀት ማጎልበት ነው፡፡ ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ የቃላት ትምህርት ለቋንቋ ተማሪ አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በተያያዘ እንደ McCarthy (1990) ገለጻ ቃላት የማንኛውም ቋንቋ ትምህርት ወሳኝ አካላት ናቸው፡፡ ቃላት መሰረታዊ የቋንቋ ትምህርት ወሳኝ አካላት በመሆናቸው አንድ ሰው በቂ የሆነ የቃላት ዕውቀት ከሌለው ሃሳቡን በተሳካ ሁኔታ ሊገልፅም ሆነ ሃሳብን ሊቀበል አይችልም፡፡ ቃላት ፍች የመሸከም ከፍተኛ የሆነ ሃይል አላቸው፡፡ ተማሪዎች ለትምህርት የቀረበላቸውን የቋንቋውን ድምፅና ሰዋሰው ቢያውቁ በቀረበበት የቋንቋውን የቃላት ዕውቀት ከሌላቸው በቋንቋ አጠቃቀም ስኬታማ ተግባቦት ለማከናወን ይሳናቸዋል፡፡ ይህ ማለት ለቋንቋ ዕውቀት ከድምፅና ከሰዋሰው ይበልጥ የቃላት ዕውቀት ወሳኝ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ ቃላት ያላቸው ጠቀሜታ አስመልክቶ wikins (1972) እንደሚገልጹት እንደ እውነት ከሆነ ያለ ሰዋሰው ዕውቀት በጠቂቱም ቢሆን ሃሳብ መግለጽ ይቻላል፤ ያለ ቃላት ዕውቀት ግን ምንም መግለፅ አይቻልም፤በጥቅሉ ቋንቋ ለመማር ቃላት መሰረታዊ ነገሮች ናቸው በማለት ይገልጹታል፡፡ ቋንቋን ለመማር ቃላት የትምህርት መሰረት መሆናቸው፤ ማንኛውም ቋንቋ የቃላት ድምር ውጤት መሆናቸው ፣ሃሳብን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ለመግለጽ ከሌላ አቅጣጫ የሚሰነዘሩ ሃሳቦችን አዳምጦ እና አንብቦ ለመረዳት በአጠቃላይ በተግባቦታዊ ክንውን መሳካት የቃላት ዕውቀት መኖር ወሳኝ መሆናቸው ነው፡፡ በአጠቃላይ እንደምሁሩ ገለጻ ቋንቋ ለመማርና ከሰዎች ጋር የተሳካ ተግባቦት ክንውን እንዲኖር የቃላት ዕውቀት ጉልህ ድርሻ እንዳለው ይጠቅሳሉ፡፡

በተያያዘ የቃላትን ዕውቀት ወሳኝነት በተመለከተ McCarthy(1990) እና Scrivener (1998) እንደገለጹት የማንኛውም ቋንቋ ትምህርት ወሳኝ አካላት ቃላት ናቸው፡፡ ቃላት ፍችን የመሸከም ከፍተኛ ሀይል አላቸው፡፡ ተማሪዎች በትምህርት በቀረበለላቸው ቋንቋ ድምፆና ሰዋሰው ቢያውቁ የቃላት እውቀት ከሌላቸው ቋንቋ ተጠቅመው ብቻ የተሳካ ተግባቦት ለማከናወን ይቸገራሉ፡፡ ስለዚህ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ቃላት ፍችን የመሸከም ቁልፍ ሚና ተተኳሪ ጉዳይ

እንዲሆን አድርጎታል፤ በማለት ከላይ ምሁራን ከጠቀሱት ሃሰብ ጋር የተያያዥነት ያለው ሃሳብ ገልጸዋል፡፡

በእያንዳንዱ ቋንቋ ውስጥ የተለያዩ ነባራዊ ነገሮችንና እሳቤዎችን ወክለው የሚገኙትም ቃላት ናቸው፡፡ ስለሆነም Nation (2001) እንደሚገልጹት ቃላትን ለማስተማር ሲታቀድ አላማው ለምን ተግባር እንደሆነ መወሰን ማለት ነው፡፡ ቃላትን ለመማር በቋንቋው ያሉ የቃላት ብዛት፣ በቋንቋ አፈፊት የሆኑቱ ምን ያህል ቃላት ይታወቃሉ? እና ቋንቋውን ለመጠቀም ምን ያህል ቃላት ያስፈልጋሉ? የሚሉትን ማወቅ ያስፈልጋል በማለት ቃላት ከማስተማራችን በፊት አላማ ሊኖረን እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡ ይህን ሃሳብ በተመለከተ Gairns እና Redman (1986) እና Harmer (1991) ሲገልጹ እንዲማሩ የሚቀርቡ የቃላት አመራረጥ የተማሪዎችን ፍላጎት፣የቃላት ተጨባጭነት ወይም ረቂቅነት፣የድግግሞሽ መጠን ባገናዘበ መልኩ ለተማሪዎች መቅረብ እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ በተያያዘ የተመረጡት ቃላት ከሚማረው ሰው ተዋህደው እንዲቀሩ አቀራረባቸው የተደራጀ መሆን እንዳለበትም ያስገነዝባሉ፡፡

ቃላትን ማስተማር በተመለከተ Macaro (2001) እንደሚገልጹት ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት ቃላትን ማስተማር ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ የቃላት ዕውቀት ለቋንቋ እና ለሌሎች ትምህርቶችን ለመማር እንገለገልበታለን፡፡ ይህ ሃሳብ አስፈላጊነቱ ታምኖበትም ለረጅም ዘመናት ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ በዚህ ሃሳብ ላይ የተለያዩ አስተያየቶች ሲሰጡ ቢቆዩም በተለይ በ17ኛው ክፍለ ዘመን አስፈላጊነቱ ታምኖበት፣ የማስተማሪያ ስልት ተቀይሶለት እንደ አንድ የቋንቋ ትምህርት ዘርፍ መሰጠት ተጀመረ የሚለው አስተያየት በብዙ ምሁራን ታምኖበት ተጠቅሷል፡፡

በተያያዘ Scholfield's (1997) እንደሚገልጹት ቃላትን የማስተማር ትኩረት እና ፍላጎት የመነጨው በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ በአብዛኛው ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከመምጣቱ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ከቅርጽ ይልቅ ትርጉም ላለው መስተጋብራዊ ተግባር አፅንዖት ይሰጣል:: በመሆኑም የቃላት እውቀት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ስኬታማ ተግባቦት ለማከናወን መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑ እንዲታወቅ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ይህ አቀራረብ ተማሪው በታላሚው ቋንቋ መጠቀም እንዲችል ማድረግ ነው፡፡ ትምህርት የሚከናወነው አራቱን ክሂሎች (ማዳመጥ፣መናገር፣ማናበብና መጻፍ) በማዳበር በመጨረሻም ተማሪው በተግባቦታዊ የመማር ስነዘዴ በየደረጃው የቋንቋ እውቀት እንዲገነዘብ ማስቻሉ ነው፡፡ ይህ ዘዴ የቃላት ችሎታቸውን ለማዳበር ተማሪዎች እንዴት ይማሩ ለሚለው የበለጠ ትኩረት ይሰጣል በማለት ይገላጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ቋንቋ ለመማር የቃላት ዕውቀት መዳበር ወሳኝነት እንዳለው የተማሪዎች የቃላት ዕውቀት ለማዳበር የሚደረግ ጥረት በመማር ማስተማር ክንውን ጥናት መሰረት ያደረገ የቃላት ትምህርት አቀራረብ እና አተገባበር ወሳኝነት አለው፡፡ በተጨማሪ የቃላት ትምህርት ለተማሪዎች ፍችን ብቻ የምናስተምርበት ሳይሆን የቃላት አጠቃቀም፣ ሰዋሰዋዊና አገባባዊ ፍችን የምናቀርብበት የቋንቋ ትምህርት ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በክፍል ውስጥ የቃላት ትምህርት አተገባበር በተመለከተ መምህራን እንዴት እንደሚተገብሩት የሚዳስስ ጥናት ነው ፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህ ጥናት በጉራጌ ዞን በቡታጀራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ የቃላት ትምህርት አተገባበር ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ አጥኚው ይህን ጥናት ለማጥናት የተነሳበት ምክንያት አጥኚው በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች አዳዲስ ቃላት ሲጠየቁ ያለመመለስ፣ የቤት ስራና የክፍል ስራ ያለመስራት በቃላት ትምህርት ዝቅተኛ የተሳትፎ በማሳየታቸው ችግሮች በተደጋጋሚ በክፍል ውስጥ በመመልከቱ ነው፡፡ የተማሪዎች ተሳትፎ መጠን ዝቅተኛ የመሆኑ ምክንያት መምህራን የቃላት ማስተማሪያ መንገዶች አተገባበር መፈተሽ ያስፈጋል በሚል ለማጥናት ተነሳስቷል፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት አላማ በጉራጌ ዞን በቡታጀራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪነት ያደረገ የቃላት ትምህርት አተገባበር ትንተና ሲሆን በዚህ አብይ አላማ ስር የሚከተሉት ጥያቄዎችን ጥናቱ ይመልሳል፡-

ሀ/ መምህራን ይበልጥ የትኛውን የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶችን ይጠቀማሉ?

ለ/ የመምህራን የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ የአተገባበር ሂደት ምን ይመስላል?

ሐ/ ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ያላቸው ተሳትፎ ምን ያህል ነው?

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በጉራጌ ዞን በቡታጀራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል መምህራን የቃላት ትምህርት እንዴት እንደሚተገብሩ በተጨማሪ ተማሪዎች መምህራን

በሚያቀርቡት የቃላት ትምህርት ያላቸውን ተሳትፎ ማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም የመምህራን አተገባበርና አቀራረብ እንዲሁም የተማሪዎች ተሳትፎ በመፈተሽ ጠንካራና ደካማ ጎኑን በመለየት ጠንካራ ጎኑን የሚበረታቱበት በተጨማሪ በቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ የሚታዩ ደካማ ጎኖች በመለየት አስተያየት ለመስጠት እንዲሁም ወደፊት በቃላት ትምህርት ላይ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ ግብአትነት ለመጠቀም ያገለግላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ዋና ትኩረቱ የቃላት ትምህርት  አተገባበር ትንተና በጉራጌ ዞን በቡታጅራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪነት ያደረገ ነው፡፡ በዚህ ጥናት በቡታጀራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርት ቤት ካሉ ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች እና መምህራን እንዲህም የቃላት ትምህርት አቀራረብ እና አተገባበር ላይ ትኩረት ሲያደርግ ሌሎች ይዘቶችን በዚህ ጥናት ላይ ትኩረት አያደርግም፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

ለተማሪዎች የቀረበው የፅሑፍ መጠይቅ በተመለከተ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን መጠይቁን ስለ ተማሪው መረጃ የሚገልፅ ፤ ስለቃላት ትምህርት  አተገባበር  በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ የሚሉ መልሶች የሚሹ በሠንጠረዥ የቀረቡ ጥያቄዎች ቢቀርቡም አንዳንድ መልሶች የመዝለልና ወረቀቶቹ ላይ ስም መፃፍ በውስንነት ታይቷል፡፡

## 1.7 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ብያኔ

የቃላት ትምህርት  አቀራረብ፡-ለትምህርት የሚቀርቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች በተማሪዎች አእምሮ የግንዛቤ አሻራሊተው በሚችልበት አኳሃንና ቃላቱን ለመጠቀም በሚያስችሉ ስልቶች (በአውድ፤በፍች  ፤በዝምድና፤ በተቃርኖና  በተመሳስሎ ) በመሳሰሉ  አጃቢነት ማሰናዳት ምልክት ነው ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

### 2.1 የቃላት ምንነት

ስለቃላት ምንነት በተመለከተ ብሩክታዊት (2001) የCooper(1997) እና Stubbs (2002) በመጥቀስ እንደገለጹት ቃል ማለት ምን ማለት እንደሆነ ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት አስቸጋሪ መሆኑ እና ስለ ቃል ምንነት በተለያዩ ጊዚያት የተለያየ ብያኔ መሰንዘሩን ገልጸዋል፡፡

ስለ ቃላት ምንነት በተመለከተ McCarthy(1990) ሲገልጹ ቃላት ትርጉም ያላቸውና ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ምዕላዶች እንደሆኑ ፤በመግለጽ ቃል እንዲባሉ አንድን ትርጉም ማስተላለፍ እንዳለባቸው ይገልጻሉ፡፡

ከላይ የምሁራኑ ሃሳብ በተያያዘ ስለ ቃላት ምንነት በተመለከተ ባዬ (2000፣72-74) እንደገለጹት ስለ ቃል ምንነት እና በቃል እና በምዕላድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በተመለከተ እንደገለጹት ቃል እንደ ምዕላድ ትርጉም ያለው መሆኑ ፤ቃል ራሱን ችሎ ስለሚቆም ነፃ ነው በዚህ ባህሪው ከምዕላድ ጋር ይመደባል፣ቃል በውስጡ ብዙ ጥገኛ ምዕላዶች ሊይዝ ይችላል፡፡ ትርጉም አዘል ወደሆነ አነስተኛ ክፍሎች ሊሸነሽን ስለሚቺል ከምዕላድ ይለያል በማለት ያብራሩታል፡፡ በአጠቃላይ የቋንቋን ትምህርት ስናስብ ደጋግመን ማስታወስ ያለብን ማህበራዊ አጠቃቀሙና የቋንቋው ውስጣዊ ሥርዓት የተዋሃዱ የመሆናቸውን ያህል፣ ስለ ቃላትም የምናስበው የአንድን ቋንቋ ሥርዓት ተከትለው የተሰደሩ በቋንቋው ተናጋሪዎች መካከል መግባባትን ሊያስገኙ የቻሉ አነስተኛና ፍች አዘል ቅንጣቶች እንደሆኑ ነው፡፡ ማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ሲባልም አንድን ፅንሰ ሀሳብ ወክሎ መልዕክትን በማስተላለፍ ረገድ ወይም ደግሞ እርስ በርስ በመግባባት ወቅት ስምምነት ተቀባይነት ያለው የቋንቋውን አካል የሚመለከት ተግባር ነው፡፡ በቋንቋ ውስጥ ቃላት ከፍች አንፃር ሲታዩ የተጠቃሚውን ማህበረሰብ ልማድ፣ ወግ፣ ባህል፣ እምነት ወዘተ መግለጫ የሆኑ በስምምነት ተቀባይነት ያገኙ የቋንቋው አነስተኛና ፍች አዘል ቅንጣቶች ናቸው ተብለው የተገለጹት ከተናጋሪው ማህበረሰብ አንፃር በመመልከት ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

በተያያዘ Ur(1996) ስለቃላት ምንነት በተመለከተ ሲገልጹ ቃል ከላይ ሲታይ የተወሰነ ፅንሰ ሃሳብ የሚወክል የድምፃች ቅንጅት ነው፡፡ አፈፊቱ የሚለምደው ኢ-አፈፊቱ የሚማረው በማለት ያብራሩታል፡፡

በአጠቃላይ በቃላት ዙሪያ የተሰጡትን ብያኔዎች እንደሚገልጹት ቃላት የሚፈጠሩት ከአንደበት በሚወጡ ድምፃች ሲሆን ድምፃቹም በስርአት መቀናጀት ይኖርባቸዋል፡፡ በመጀመሪያ ድምፃቹ ትርጉም አልባ ይሁን እንጂ በቋንቋ መዋቅራዊ በስርአት ከተሰደሩ ትርጉም አዘል የሆኑትን ቃላት ይመሰርታሉ፡፡ ቃላት ትርጉም ይመስርቱ እንጂ አመሰራረታቸው የድምፃች ፣የምዕላዶች እና የቃላት የእርስ በርስ ቅንጅት ውጤት ነው፡፡

## 2.2 ቃላትን የማስተማርና አስፈላጊነት

ቃላትን ማስተማር በተመለከተ Nation (2001) እንደገለጹት በመጀመሪያ ቃላትን ለማስተማር ሲታቀድ ቃላት የመማር ግቡ ምንድነው? የሚለውን መለየት ይኖርበታል፡፡ ይህም ተማሪው ቃላቱን ለምን ተግባር እንደሚጠቀምበትና እንዲረዳ ያግዘዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪው ቃላትን ለምን ተግባር እንደሚጠቀምበት ከተለየ ለዚህ ተግባር ምን ያህል ቃላት መማር ይጠበቅበታል? ለሚለው መረጃ ለማግኘት የሚረዱ ሶስት ሁኔታዎች አሉ፡፡ እነዚህም በቋንቋው ያሉ የቃላት ብዛት፣ በቋንቋው አፈፊት የሆኑቱ ምን ያህል ቃላት ይታወቃሉ እና ቋንቋውን ለመጠቀም ምን ያህል ቃላት ያስፈልጋሉ የሚሉት ናቸው በማለት ይገልጹታል ፡፡

በተመሳሳይ Harmer(1991) እንደገለጹት ሰዋሰዋዊ መዋቅሩ የቋንቋውን አፅም ሲመሰርት ቃላት ደግሞ ወሳኝ የሆኑትን የቋንቋውን ብልቶች ማለትም ስጋና ደም ሆነው ሕይወት እንዲዘራ ያደርጉታል በማለት ይገልጹታል፡፡ በተመሳሳይ የቃላት ወሳኝነት ሚና በተመለከተ McCarthy (1990) እና Scrivener (1998) እንደገለጹት የማንኛውም ቋንቋ ትምህርት ግዙፍ አካላት ቃላት ናቸው፡፡ ቃላት ፍችን የመሸከም ከፍተኛ ሀይል አላቸው፡፡ ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ድምፃችና ሰዋሰው ተማሪው ቢያውቅ በተጨማሪ የቃላት እውቀት ከሌለው የተሟላ ተግባቦት ማከናወን አይችልም፡፡ በቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ቃላት ፍችን የመሸከም ሚናቸው በቃላት ጥናት ተተኳሪ እንዲሆን አድርጎታል በማለት ይገልጹታል፡፡

ቃላትን ማስተማር ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ይህም የቃላት ዕውቀት ለቋንቋም ሆነ ሌሎች ትምህርቶችን ለመቅሰሚያነት እንገለገልበታን፡፡ ቃላትን ማስተማር ጠቀሜታው ታምኖበትም ለረጅም ዘመናት ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ በዚህም ጉዳይ

የተለያዩ አስተያየቶች የተሰጡ ቢሆንም በተለይ በ17ኛው ክፍለ ዘመን የማስተማሪያ ስልት ተነድፎለት እንደ አንድ የቋንቋ ትምህርት ዘርፍ መሰጠቱ በብዙ ምሁራን ተገልጻል፡፡ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መሠረት የጣለው ይህ የቃላት ትምህርት ሁኔታ እየተስፋፋና እያደገ ከመሄድ ይልቅ ጭራሹንም ለረጅም ጊዜ ተረስቶ እንደገና ማንሰራራት የጀመረው ከ1970ዎቹ ወዲህ እንደሆነ በዘርፉ የተሰማሩት ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

እንደ Harmer (1991) እና Nunan(1991) ገለጻ ለቃላት ትምህርት ለረጅም ጊዜ ተረስቶ የመቆየት በምክንያትነት ከሚጠቀሱት መካከል በሥነ-ልሳን ዘርፍ ይሰጡ ከነበሩት የተለያዩ የአመለካከት አቅጣጫዎች ይገኙባቸዋል፡፡ በተለይም ለቋንቋ ትምህርት ወሳኙ ሰዋሰዋዊ ሥርዓትን ማወቅ የሚለው ሥነ-ልሳናዊ እሳቤ ለቃላት ትምህርት መዳከም መንስኤ ሊሆን ችሏል፡፡ ቃላት አገልግሎታዊና ሙያዊ ሰዋስዋዊ ባህርያት አሏቸው፤ ይሁንና ቃላት የያዟቸውን ይህን ሰዋሰዋዊ ባህርያት መገንዘብ ሌላው ስለ ቃላት ትምህርት ያለንን ዕውቀት ያሰፋልናል፡፡ በቃላት ረገድ ከተመለከትንም ከፍች አኳያ የቃላት ንበት ፣ጥብቀትና መላላት ፣ የድምፅ ከፍና ዝቅ፣ አገባብ፣ እማሬያዊ ና ፍካሬያዊ ፍችዎች ያሏቸው መሆናቸውን ማወቅ ለአንድ የቋንቋ መምህር አስፈላጊ ከሆኑት መካከል የሚካተት ጉዳይ ይሆናል፡፡ በማንኛውም የቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ቃላትን የምንማርባቸውም ሆነ የምናስተምርባቸው በርካታ መሠረታዊ ምክንያቶች ይኖራሉ፤ ከእዚህ መካከል ጥቂቶቹ፡-

1. ቃላት ሐሳብን በማስተላለፍ ሂደት ውስጥ ቀዳሚውን ሚና የሚጫወቱ መሆናቸው፣
2. ቃላት የሀሳብ /idea/ ተሸካሚዎች የሆኑ ቁልፍ የቋንቋ አካላት መሆናቸው፣
3. ሐሳብ ከሌለ ቃል /ቃላት/ም የማይኖሩና ለቃላት መከሰቻም ብቻ ሳይሆን የሀሳብ ህላዌ መሆናቸው፣
4. ቃላት ለቋንቋ ትምህርት ማራመጃ የጀርባ አጥንቶች መሆናቸው ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ሌላው ስለቃላት ትምህርት አስፈላጊነት ምንውየለት(2005) የPikulski እና Tempieton (2004) ጠቅሰው እንደገለጹት ቃላት እለት ከእለት በመናደርገው አጠቃላይ መስተጋብር ማለትም ሃሳብ መለዋወጥን፣መልዕክት ማስተላለፍን ፣ጥያቄ ማቅረብና የመሳሰሉት ነገሮች ለማሳካት የምንጠቀምባቸው ሁለገብ የቋንቋ መሰረታዊ ጉዳዩች ናቸው፡፡ በዚህም በቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ የቃላት እውቀት ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በመሆኑም በመናገር ፣በማዳመጥ ፣በማንበብ

እና በመፃፍ ለመግባባት ቃላት ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡ ተማሪዎች በቋንቋው የሚፈጥሩት ተግባቦት የጠራ እና የተቀላጠፈ ይሆን ዘንድ ቃላት ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡በቋንቋ መጋባባት ሂደት ውስጥ የቃላት እውቀት ቁልፍ ሚና እንዲሚጫወት አብራርተዋል፡፡

በተያያዘ Wallace(1988፤9፣27) የአንድ ቋንቋ ስርአት እንዴት እንደሚሰራ በጥሩ ሁኔታ ማወቅ እየተቻለ በቋንቋ ለመግባባት የሚያስችል እውቀት ላይኖር ይችላል፤ የምንፈልጋቸው ቃላት የሚኖሩን ብዙንጊዜ እንደነገሩም ቢሆን በቋንቋ መግባባት ይቻላል፡፡ በተያያዘ በቋንቋ ትምህርት ቃላት ቁልፍ ሚና አላቸው እነሱም፡- በንግግር ወቅት የቃላት ትክክለኛ ቅላፄ እንዲጠቀሙ፤የቃላት የንግግር ወይም የፅህፈት ቅርፅ ለመለየት ፤የቃላት እማሬያዊናፍካሬያዊ ፍች እንዲገነዘቡ፤የቃላት ትክክለኛ ዘይቤያዊ አጠቃቀም እንዲገነዘቡ ፤ቃላት ከሚወክሉት ቁስና ፅንሰ ሃሳብ ጋር ማዛመድ እንዲችሉ፤ቃላትን በተገቢው ሰዋሰዋዊ ቅርፅ እንዲጠቀሙባቸው፤ የቃላት ተገቢውን የመደበባኛነት ደረጃ ጠብቀው እንዲጠቀሙ ይረዱቸዋል በማለት ይገልፃሉ፡፡

ምንውየለት (2005) የCarter እና McCarthy(1988፣45) በመጥቀስ እንገለጹቸው የቃላት ትምህርት በመርሐ ትምህርት ታቅፎ በቋንቋ መማሪያ ስፍራ ተሰጥቶት በትምህርትነት ሲቀርብ ቢቆይም ቃላትን ለማስተማር ተገቢ የሚሆነውን ዘዴና ስልት ማፈላለግ ተዘንግቶ የቆየ ተግባር ነው፡፡ የቃላት ትምህርት ከ1970ዎች በፊት ራሳቸውን የቻሉ የቋንቋ ትምህርት አካላት ተደርገው አይታዩም ነበር፡፡ ስለዚህ የቋንቋ ትምህርት የታላሚውን ቋንቋ መዋቅር ጠንቅቆ በማውቅ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላትም የቋንቋውን መዋቅር ለማሳየት አስፈላጊ የሆኑት ብቻ ነበሩ በማለት ይገላፃሉ፡፡ በጊዜው ከነበሩ የተግባራዊ ስነልሳን ምሁራን ተማሪዎች መሰረታዊ የሆኑ አወቃቀሮችን ከለዩ በዋላ ሰፋ ያለ የቃላት እውቀታቸው ቀስ በቀስ ሊገነባ ይችላል የሚል እምነት ነበራቸው፡፡ በዚህም ትኩረታቸውን ያሳረፉት የቋንቋ መዋቅር ለማስተማር አስፈላጊ በሆኑ ቃላት መረጣና የቋንቋ ለመዳውን ለማፋጠን ያግዛል ባሉት በንፅፅራዊ ጥናት ትንተና ላይ ነበር ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የቃላት ትምህርትን አስፈላጊነት የመዘንጋት ሁኔታ ሊቀጥል አልቻለም፡፡ ከ1970ዎቹ በዋላ በነበሩት ጥቂት አመታት ውስጥ የቃላት ትምህርት በቋንቋ መማር ውስጥ ተገቢ ቦታውን እያገኙና እንደ ክሂል እየተቆጠሩ የመምጣቱ ሁኔታ እውን ሆኗል በማለት ይገላጻሉ፡፡

ስለቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ስልቶች በተመለከተ ምንውየለት (2005) የAllen (1983፣5) በመጥቀስ እንደገለጹት የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ስልቶች ከፍተኛ ትኩረት መሰጠቱ ሁለት ምክንያቶችን ይጠቅሳሉ፡- እነሱም መምህራን ቃላትን ለማስተማር ብዙ ጊዜ ያባክኑ እንደነበር

እና ተማሪዎች በቋንቋ ተግባቦት የመፍጠር ችግር ምንጩ ከቃላት ጋር የተያያዘ መሆኑ የሚሉት ናቸው፡፡ የቃላት ትምህርት ፋይዳ የቃላትን ትርጉም ከማወቅ ባሻገር ለሌሎቹ የቋንቋ ዘርፎች ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡

በተያያዘ Maley (1990፣10) እና Tayior (1990፣1-7) ስለ ቃላት ትምርህት አስፈላጊነት ሲገላጹ ቃላት በተሟላ መልኩ ማወቅ የሚሉትን ያካትታል፡- የቃላት የንበት ቅርፅ ለመለየት፤በቋንቋ ውስጥ ያለውን የድግግሞሽ መጠን ለማወቅ፤የቃሉን የፅህፈት ቅርፅ ለማወቅ፣ውስን አገባቡን ወይም አውዱን ለመገንዘብ፤ የቃሉን የንግግር የእርባታ ክፍል ለመገንዘብ ፤ስነ አገባባዊ ና ስነ መዋቅራዊ ቅደም ተከተሉን ለመለየት እና የቃሉን መሰረታዊ ፍች ለማወቅ ይረዳል ፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን ይዘቶች ተማሪዎች ከተገነዘቡ በተግባቦት ወቅት ሊፈጠሩ የሚችሉትን ተግዳሮቶችን ማስወገድ ይችላል፡፡

የቃላት እውቀት በተግባቦት ሂደት ውስጥ ያለውን ጉልህ ሚና በመለከተ McCarthy (1990) ሲገልጹ፤ የቋንቋውን መዋቅር ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ በሚማሩት ጉዳይ ብቻ የሚጠቅመው ነገር የለም፤ የተሳካ ተግባቦት ለማከናወን መሠረታዊው ነገር የቃላት እውቀት መኖር ነው፡፡ ይህም ሲባል ተማሪዎች በቋንቋው የተፃፈን ነገር አንብቦ መረዳት ፣ቃላት በመመስረት እና በማራባት እንዲሁም ንበቱን በመገንዘብ ስነ አገባባዊ እና ስነ መዋቅራዊ ቅደምተከተልን በመጠበቅ ለመፃፍ፣ የሚነበብና የሚነገርን መልዕክት ሳይዛባ ለመገንዘብ በተጨማሪም የቋንቋውን ሰዋሰው ለመገንዘብ የቃላት ሁለንተናዊ ዕውቀት መኖር ተገቢ እና አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት የቃላት ትምህርት ከሌሎቹ የቋንቋ ዘርፎች በበለጠ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን መረዳት እንችላለን በማለት ያብራራሉ፡፡

## 2.3 የቃላት ትምህርት ማስተማሪያ መርሖች እና ማቅረቢያ መንገዶች

### 2.3.1 የቃላት ትምህርት ማስተማሪያ መርሖች

ዘሪሁን (1996፣82-83) እንደገጹት የቃላት ሀሳብን የማስተላለፍ ደረጃና አቅም የተለያየ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ሁሉም ቃላት እኩል የገላጭነትና የስዕላዊነት አቅም አይኖራቸውም፡፡ አንዳንድ ቃላት ሰፉያለ ሀሳብን አምቆ የመያዝ ችሎታ ሲኖራቸው፤አንዳንዶቹ ተራ በመሆናቸው አቅም ያነሳቸው ሆነው ይገኛሉ፡፡ አንዳዶች ደግሞ ምስል የመከሰት አቅማቸው ብርቱ ሲሆን የቀሩት ደግሞ ሃሳቡን ጭራሽ የሚያደበዝዙ ይሆናሉ በመሆኑም የቃላትን ትምህርት ስናስተምር ቃላት ላይ ትኩረት ማድርግ እንዳለብን ይገልፃሉ፡፡

የቃላት ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲተገበር መሪ የሆኑ የቃላት ማስተማሪያ መርሖዎች እና ዘዴዎች እንደሚያስፈልጉ ምሁራኑ ይጠቁማሉ፡፡ ብሩክታዊት(2001) በጥናቷ መምህራን የቃላት ትምህርት ከማስተማራቸው በፊት ሊገነዘቧቸው የሚገቡ መርሖች ይኖራሉ፡፡ እነዚህም፡-

ሀ/ዓላማ፡- መምህራን በቃላት ትምህርት ሂደት የትኞቹን ቃላት ለምን አላማ እንደሚያስተምር ማወቅ አለበት፡፡ ስለዚህም ዓላማ በቃላት ማስተማር መርሖች ውስጥ ቀዳሚ ነገር ነው::

ለ/ወሰን፡-በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ የቃላት ብዛት ለመወሰን መምህራን ማጤን እንደሚገባቸው ፤የቃላቱን ፍች ተጨባጭ ከማደረግ አንፃር በመርጃ መሳሪያ ሊደገፍ መቻሉ፤ለትምህርት የቀረበው ቃል ከተማሪው አፍ መፍቻ ቃላት ጋር ያለው የቅርፅ ተመሳስሎ ምን ያህል ስለመሆኑ፣ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ፣ከክፍለ ጊዜው ርዝማኔ ጋር ተመጥነው መቅረባቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ለታላሚው ቋንቋ ቃላት ተማሪዎች ለበርካታ ጊዚያት ማጋለጥ ከተማሪዎቹ ጋር ተዋህደው እንዲቀሩ በማድረግ ረገድ ጠቃሜታው የጎላ ነው፡፡

ሐ/ብዙ ጊዜ ለቃላት ማጋለጥ፡- ተማሪዎች የተሟሯቸውን ቃላት በተለያየ ጊዜ እየደጋገሙ እንዲገለገሉባቸው በማድረግ ለትውስታ በሚመች መልኩ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

መ/ ሁኔታዊ አቀራረብን መከተል፡- የቃላት አቀራረብ እንደ ቀረቤታ፣የዕውቀት ደረጃ፣እንደ ቦታውና ዕድሜ ይለያያል፡፡ በማምለኪያ ስፍራዎች፣ በመዝናኛቦታዎች፣ በጤና መስጫ ስፍራዎች፣ወዘተ. ተግባር ላይ የሚውሉ ቃላት ይለያያሉ፡፡ ተማሪዎች እነዚህን በተለያዩ ሁኔታዎች ውሰጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ተገቢ ቃላትን መማር ይኖርባቸዋል፡፡ በቃላት አጠቃቀም ውስጥ የመደበኛ እና የኢመደበኛ ቃላት አጠቃቀምን በድራማ እና በሌሎች መልኩ መምህሩ ማስተማር ይችላል፡፡

ሠ/ ቃላትን በአውድ ማቅረብ፡- በቃላት ትምህርት ወስጥ ቃላት ከሌሉች ቃላት ጋር እንዴት እንደሚገቡና አዘውትረው ከየትኛቹ ቃላት ጋር እንደሚመጡ ማስተማር አስፈላጊ ጉዳይ ነው:: እያንዳንዱ ቃል በዐውድ ሲቀርብና ከዐውድ ውጪ ሲሆን ተለያየ ፍች ሊኖረው ይችላል፡፡

ረ/ ቃላትን ለትንበያ በሚመች መልኩ ማቅረብ ፡- የቃላትን ፍቺ ለመገመት ቃሉ የገባበትን ዓረፍተነገር ደጋግሞ በማንበብ፣የቃሉ ቅድመ ግንድ ቅጥያ፣ድህረ ግንድ ቅጥያ በመለየት ይህ

ካልተሳካ መዝገበ ቃላትን በማገላበጥ፣ሰውን በመጠየቅ፣ ወዘተ. የቃላትን ችሎታን ማሳደግ ይቻላል። ተማሪዎች የታላሚው ቃላት ችሎታ የሚያሳድጉት በቀረበላቸው አውድ ውስጥ የቃላትን ፍቺ መተንበይ መቻልን ሲማሩ ነው። መምህራን ተማሪዎቻቸው የቃላት ችሎታቸውን በራሳቸው ጥረት እንዲያሳድጉና እንዲማሩ በዐውድ ውስጥ ቃላት እንዴት ፍቺቸውን መተንበይ እንዳለባቸው ማለማመድ ይገባል።

ሰ/ይዘትን መወሰን፡- በቃላት ትምህርት ውስጥ የምናስተምረው የቃላት ይዘት መወሰን ቀዳሚው መርህ እንደሆነ በመግለፅ ቃላት ለመምረጥ ዋና ዋና መስፈርቶች የሚባሉት የድግግሞሽ መጠን፣ ባህላዊነት እና ከተማሪው ፍላጎትና ችሎታ ጋር መጣጣም የሚሉት ናቸው።

ሸ/ ቃላትን ማቧደን፡-ቃላትን በተመሳሳይ ባህሪያቸው ማቧደንን ለትውስታ እጅግ አመቺ በመሆኑ በዚህ መልክ ማስተማሩ ተመራጭ ነው። ቃላትን በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ፣ በሚኖራቸው የፍች ተዛማዶ እና የፍች ተቃርኖ ማቧደን ይቻላል በማለት ብሩክታዊት(2001) የWallace(1982፤27-35)፤Cooper (1997፤236)፤Gaims እና Redman (1986፤59) እና McCarthy (1990፤60) ጠቅሰው ገልጸዋል።

## 2.3.2 የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች

እንደ Grains እና Redman (1986) ገለጻ ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላት በተማሪዎች አዕምሮ ውስጥ ሰርፀው በሚገቡበትና በሚታወሱበት አኳኋን መቅረብ ይኖርባቸዋል። ይህ እንዲሆን ደግሞ የሚቀርቡት ቃላት የተማሪዎችን እድሜ፣ የትምህረት ዳራ፣ የትምህርቱን ዓላማ፣ የአዳዲስ ቃላትን ባህሪ፣ ያገናዘቡና ቃላቱን ለመጠቀም በሚያስችሉ ስልቶች የዳበሩ የቋንቋ መልመጃዎችን መሰረት ያደረጉ መሆን ይኖርባቸዋል። የቃላት እውቀት የቃላትን ፍች ከማወቅ በላይ የዘለለ ነው። ይኸውም ተማሪዎች ባሰቡትና በፈለጉት መንገድ ሃሣባቸውን ለማስተላለፍ የቃላት ብቃት ያሻቸዋል። የቃላት ብቃት ሲባልም የቃላትን ፍች ማወቅን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የቃላት አጠቃቀምና ሰዋስዋዊ ቅርፅን የሚያቅፍ ነው። ስለዚህም የቃላት እውቀት ፍችን ከመገንዘብ በላይ የሆነ የብዙ እውቀቶች ድምር ውጤት ነው።

ስለቃላት ማስተማር በተመለከተ Wallace (1988)፣ Harmer(1991፤156) እና Ur (1996፤60) ሲገልጹ የቃላት ትምህርት ለተማሪዎች ፍችን ብቻ የምናስተምርበት ሳይሆን የቃላት አጠቃቀም፣ ሰዋሰዋዊ ፋይዳውንና አገባባዊ ፍችን የምናቀርብበት የቋንቋ ትምህርት ዘርፍ ነው።

የቃላት እውቀት ፍችን ከመገንዘብ በላይ እንደሆነና የበርካታ ዕውቀቶች ድምር ውጤት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

Morgan(1986፣3) እንደገለጹት ቃላት አንድ ነጠላ ትርጉም ብቻ ይዘው የምናገኛቸው ሳይሆኑ እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ ፣ በትስስሮሹ ሳቢያም የተለያዩ ቅርፆችንና ፍችዎችንም የሚይዙ ናቸው፡፡ ስለዚህም ተማሪዎቹ አዳዲሶቹን ቃላት ከቀደመ እውቀታቸው ጋር እያገናዘቡ የማሰብና የመተንበይ ችሎታቸውን እየተጠቀሙ ቅርፃቸውን ከፍቻቸው ጋር ሊያውቁ በሚችሉበት ሁኔታ ሊቀርቡ ይገባል፡፡ የተለያዩ ምሁራን የቃላት ትምህርት እንዴት እንደሚለመዱና እንደሚዳብሩ በሚያሳይ መልኩ በጠንካራ እሳቤዎች ላይ በመመስረት፤መቅረብ አለባቸው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከላይ ከቀረቡት የምሁራኑ ገለፃ መረዳት የሚቻለው ቃላት በትምህርትነት ሲቀርቡ የተማሪውን እድሜ፣ ባህል፣ የትምህርት ዳራና የትምህርቱን ዓላማ ባገናዘበ መልኩ መሆን እንዳለበትና ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላትንም በተለያዩ አውዶች ውስጥ በተደጋጋሚ ሊያገኟቸው እንደሚገባ ነው፡፡

በቃላት የመማር ሥልቶች ላይ እስከዛሬ የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የቃላት ማቅረቢያ ዘዴዎችን አስተዋውቀዋል፡፡ ከእነዚህ የቃላት ማቅረቢያ ስልቶች መካከልም ዋና ዋና የሚባሉት ቃላትን በአውድ ማቅረብ፤ ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው ማቅረብ(ቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍቺ ማቅረብ፣የቃላት አካታች ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ እና የቃላት አብሮ ተሰላፊነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ)፤ የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ማቅረብ፤ የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ፤ ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ ፣ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳት ና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ ፤ቃላትን ግልፅ በሆነ መመሪያዎችን ማቅረብ እና ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ማቅረብ የሚሉት ናቸው፡፡

### 2.3.2.1 በአውድ ማቅረብ

እንደ Nation እና Coady (1988 ፣102) ገለጻ አውድ በአጠቃላይ ገፅታዎች ሊከፋፈልና ሊገለፅ የሚችል ሆኖ በአንድ በተሰጠ ውህድ አሀድ (ፅሁፍ ወይም ንግግር) ውስጥ እንደ ሥነ ምዕላዳዊ፣ ሥነ አገባባዊና ዲስኩራዊ መረጃ ሊታይ ይችላል ይላሉ፡፡ የውህድ አሀዱ አንባቢ ወይም አድማጭ ውህድ አሀዱ ስለሚናገረው ጉዳይ የራሱ የሆነ ዳራዊ እውቀት ይኖረዋል፡፡ በአጠቃላይ አውድ ውስጥ እንደሚጠቃለል ይገልጻሉ፡፡

በተያያዘ Harmer (1991) እንደገለጹት አውድ ማለት ቋንቋ በጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ የሚያመቻች ሁኔታ ወይም የመረጃ ጥንቅር ማለት እንደሆነ በማስረዳት ከ Nation(1988) ጋር ተቀራራቢ ብያኔ ይሰጣሉ፡፡ Harmer(1991) አውድን በሁለት መንገድ ይመለከቱታል፡፡ አንደኛው አውድ አንድ ንግግር የፈለቀበትን ሁኔታ የሚያሳይ ሲሆን ይህም ሁኔታዊ አውድ ሊባል ይችላል፡፡ ሁለተኛው፣ አንድ ንግግር የፈለቀበትን ሥነ ልሳናዊ አካባቢ የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሥነ ልሳናዊ አውድ ይባላል፡፡ እነዚህ ሁለቱም የአውድ አይነቶች ቃላትን መርጦ ሃሣብን በማስተላለፍ ሂደት ላይ የየራሳቸው ተፅዕኖ አላቸው፡፡ አውድ ለቃላት ትምህርት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ይኸውም ቃላት ከሥነ ልሳናዊም ሆነ ከሥነ ልቦናዊ እይታ አንፃር ፍቻቸው ግልፅ የሚሆነው በተገቢው አውድ ውስጥ ሲገቡ ነው፡፡

Cunnings-worth(1995)ተማሪዎች አንድን ቃል ያለችግር እንዲገለገሉበትና ስለፍችው በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከተፈለገ በተቻለ አቅም ቃሉን በተደጋጋሚ በተለያየ አውድ ውስጥ ሊያገኙት ይገባል ፡፡ለምሣሌ "ደረሰ" የሚለውን ቃል በተለያዩ አውዶች በማስገባት ምን አይነት ፍቺ እንዳለው፣ በምን አይነት አውድ ሊከሰት እንደሚችል፣ ከሌሎች ቃላት ጋር ያለው መዋቅራዊ ዝምድና፣ የቃሉን ሰዋስዋዊ ባህሪ ወዘተ. ለመገንዘብ በእውናዊ አውድ በማቅረብ ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም

"አለሙ ጥሩ የአማርኛ ልቦለድ መፅሃፍ ደረሰ".( ፃፈ)

"አለሙ እስብሰባው ቦታ በሰዓቱ ደረሰ"፣ ( ተገኘ፤ በሰዓቱ ቀረበ)

"አዝመራው በጊዜ ደረሰ"፣ (ለእህልነት በቃ)

"አለሙ ለአቅመ አዳም ደረሰ"(ትልቅ ሆነ፤ አደገ)

"አለሙ ለቅሶ ደረሰ" ወዘተ. በመሳሰሉት አውዶች በማስገባት በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ ይቻላል፡፡

ጌታሁን (2011)የ River (1994፣13) ጠቅሰው እንደገለጹት አንድን ቃል በተናጠል ከማቅረብ ይልቅ ተማሪዎች በድርጊት እየተሳተፉ በሚማሩበት አውድ ውስጥ ማቅረብ ትምህርቱን እንዳይረሳ ከማድረግ አኳያ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ በመሆኑም የቃላት ትምህርት አቀራረብ ቃላትን በገቡበት አውድ መገመት በሚያስችል መንገድ መሆን አለበት፡፡ ተማሪዎች ራስ አገዝና ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ ቃላትን በተገቢው አውድ አቅርቦ ማለማመድ ተገቢ ነው፡፡

በአውድ ከሚቀርቡት ቃላት መካከል ከሃያዎቹ አስራ ዘጠኙ የሚታወቁ መሆን አለባቸው፡፡ ይህም የቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው በመገመት በቀላሉ ለመገንዘብ ያስችላቸዋል፡፡

አንድ ሰው ለተለያየ ሁኔታ እና ለተለያየ ሰው የተለያየ ቋንቋ ይጠቀማል፡፡ ለምሣሌ አንድ ሰው አንድን ጉዳይ ለአለቃውና ለጓደኛው በተመሳሳይ ቋንቋ አያብራራም፡፡ እንደዚሁም ሀዘን ቤትና ሠርግ ቤት ተመሣሣይ ቋንቋ አይጠቀምም፡፡ በሌላ በኩል ሃሣብን በመግለፅ ሂደት ቃላት ብቻቸውን አይከሰቱም በሥነ ልሳናዊ አውድ ታጅበው (ከሌሎች ቃላትና ሀረጋት ጋር አብረው) ነው፡፡ መልዕክቱ ማስተላለፍ ለተፈለገው ተስማሚ በሆነ የቃላት ምርጫ ፍችን በመፍጠር ውስጥ የሚመጣ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ ስነ ልሳናዊ አውድ የቃላት ምርጫን በመደገፍ ወይም በመገደብ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ ሁኔታዎች የሚያሳዩት ሁኔታዊም ሆነ ሥነ ልሳናዊ አውድ በቋንቋ አጠቃቀም ላይ ያለውን ብርቱ ተፅዕኖ ነው፡፡ ይህም ፍችን ግልፅ ለማድረግ በሥነ ልሳናዊ አውድ ውስጥ ከየትኛው ቃል ጋር አብሮ ይሰለፋል? ምን አይነት የዲስኩር አያያዥ ሥራ ላይ ይውላል? የዲስኩር አያያዙን ተከትሎ ምን አይነት ፍች በምን አይነት ቃል ይተላለፋል? የሚሉትን ነጥቦች ሁሉ የሚመለከት ነው፡፡ አንድ ተማሪ አንድን ቃል ከአገባቡ ለመረዳት የሚከተሉትን መተግበር ይኖርበታል፡፡

•የቃል ክፍሉን መለየት

•አውዱን በሚገባ መረዳት

•የግምቱን ትክክለኛነት ማረጋገጥ

•የቃሉን ትርጉም መገመት እና

•በአውዱ ውስጥ ያሉትን ፍንጮች መፈተሽና መገንዘብ የሚሉት ናቸው፡፡ከላይ እንደቀረበው የቃላትን ትክክለኛ ፍች በአውዳዊ ፍንጮች አማካይነት መገመት ይቻላል፡፡

በተያዘ ጌታሁን (2011) የNattinger(1988)፣ Nunan(1998) እና Ying(2000) በመግለጽ ቃላትን በአውድ ውስጥ መገመት የሚያስችሉ የተለያዩ ፍንጮች እንዳሉ በመግለፅ እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፡፡

• የሥነ ምዕላድ ፍንጭ፡- የአዲሱን ቃል ውስጣዊ ሥነ ምዕላዳዊ ገፅታ (የቃሉን ግንድ፣ መነሻና መድረሻ ቅጥያ) መመርመር፣

• የብያኔ ፍንጭ፡- ቃሉ በውህድ አሀዱ (በፅሁፋ ወይም በንግግሩ) የተሰጠው ብያኔ ካለ ፍቺውን ከብያኔው መገመት፣

• ዝርዝር ምሣሌዎች በመስጠት፡- ይህ ዋናው ቃል ከሌሎቹ ፅንሰ ሃሣቦች ካላቸው ቃላት ጋር ዝምድናውን በማሳየት ማቅረብ፣ ለምሣሌ ጥቅል ፅንሰ ሃሣቡና የያዘው ቃል "እንስሳት" የሚለው ቃል ቢሆን በስሩ "ውሻ፣ ላም፣ ፍየል፣ ዓሣማ ወዘተ." የሚሉትን ዝርዝር ቃላት ማንሳት ይቻላል።

• የተመሣሣይና ተቃራኒ ቃላት ፍንጮች፡- የአዲሱን ቃል ተቃራኒ ወይም ተመሣሣይ ፅንሰ ሃሣብ የያዙ ቃላትን በተለያዩ የማቅረቢያ መንገዶች በመጠቀም ፍንጭ መስጠት ይቻላል።
•የትንበያ ፍንጭ፡- በቀረበው ዐረፍተነገር፣ አንቀፅና ፅሁፍ ላይ በመመስረት የአዲሱን ቃል ፍቺ ለመገንዘብ የሚጠቅሙ የማጠቃለያ ፍንጮች በመጠቀም አንባቢው ከቀድሞው እውቀቱ ጋር በማገናኘት የሚረዳበት ሂደት መፍጠር፣

• የንፅፅርና የአማራጭ ፍንጮች፡- አዲሱን ቃል ከሌላ ቃል ጋር በማንፃፀር ወይም በቃሉ ሌላ አማራጭ በመስጠት የቃሉን ፍቺ መገመት፣

### 2.3.2.2 ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት ማቅረብ

Wilkins (1972) እንደገለጹት ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆነውን የቃላት እውቀት ለማስጨበጥ የአዳዲስ ቃላት ፅንሰ ሀሳባዊና አገልግሎታዊ ልዩነቶችን በሚያሳይ መንገድ ማቅረብ ይገባል። የቃላት ዝምድና ከሚታይባቸው መንገዶች አንዱ ፍች ነው። የቃላት ፍቻዊ ተዛምዶ ሲባል ቃላቱ ከሌሎች ቃላት ጋር በፍች መመሳሰል፣ መቃረን ወይም የአንደኛው ቃል ፍች በሌላኛው ውስጥ መጠቃለል ምክንያት የሚፈጠረውን ዝምድና ይመለከታል። ቃላትን በመማር ሂደት ውስጥ ከተጠቀሱት ተዛምዶዎች አንፃር አንድ ላይ ማቅረቡ በቃላት እውቀት ውስጥ የሚያበረክተው አስተዋፅኦ አለው። ከሚያበረክተው አስተዋፅኦ ውስጥ በተቀራራቢ ቃላት መካከል ያለውን የፍች ልዩነት በግልፅ ለማወቅ ማስቻሉ ተጠቃሽ ነው በማለት ይገልጻሉ።

ምንውየለት(2005) የBahuer(1998) ጠቅሰው እንደገለጹት ቃላትን በተመሳስሏቸውና በተቃርኗቸው በቃላት አካታች ተከታች ግንኙነት እንዲሁም በኣብሮ ተሰላፊነታቸው ለይቶ ማቅረብ ተገቢ ነው በማለት ይገልጻሉ።

#### 2.3.2.2.1 ቃላትን በተመሳሳይ እና በተቃራኒ ፍች ማቅረብ

ጌታሁን(2011) የAllen (1983) ስለ ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት ሲገልጹ በቃላት መካከል ፍፁም የሆነ ተመሳሳይነት የለም፤ምክንያቱም ቃላት በፍች ተመሳሰሎ ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም አውድ አንዱ ቃል ሌላውን ሊተካ አይችልም በማለት ይገልጻሉ። እንዲሁም ቃላት በተወሰነ መልኩ የሚመሳሰልበትና የሚለያዩበት መጠነኛ ባህሪ አላቸው። ይህም ማለት የአንዱ ቃል የሰፋ ፅንሰ ሀሳብ መያዝ አንዱ በገባበት ሌላ አለመግባት ፣ ሰዋሰዋዊ ባህሪያቸው መለያየት ወዘተ የሚሉት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ በማለት ያስረዳሉ። በተያያዘም Grains እና Redman (1986፣23) እንደሚገልጹት ሁለት ቃላት ፍፁም በሆነ ተመሳሳይነት ማገልገል የሚችሉ ቢሆንም በቋንቋው ውስጥ የሚኖራቸው ተፈላጊነት አጠያያቂ ይሆን ነበር በማለት ከላይ ያለውን ሀሳብ ያጠናክሩታል።

የቃላትን ተቃራኒ በተመለከተ ደግሞ በአንድ ቋንቋ ውስጥ በቃላት መካከል የተለያየ የተቃራኒ አይነቶች እንዳሉ ይታወቃል። ከነዚህ መካከል Carter እና McCarthy (1988፣23-24) ሲገልጹ የደረጃ ተቃርኖ ፣የተገላቢጦሽ ተቃርኖ ፣የተፃራሪ ተቃርኖ እና አቅጣጫ ጠቀስ ተቃርኖ በማለት ጠቅሰዋል። የፍች ተቃራኒነት ሲባል የአንደኛው ቃል ፍች ሲገለፅ በአንፃሩ ያለውን ስሜት የሚያመጣ ማለት ነው። ለምሣሌ ደግ እና ክፉ፣ ቅርብ እና ሩቅ፣ ወንድ እና ሴት ዓይነት ግንኙነት ያላቸው በተቃራኒነት የሚፈረጁ ናቸው። ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎችንም የቃላት ፍች ተቃርኖዎች በጥንቃቄ በሚነደፉ መልመጃዎች አማካይነት ማቅረብና ተማሪዎቹ እንዲመረምሯቸው ማድረግ፤ቃላቱ ያሏቸው የፍች ግንኙነት ገደብ እስከምን ድረስ እንደሆነ ለመረዳት እንዲችሉ ያግዟቸዋል።

#### 2.3.2.2.2 የቃላት አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ

የቃላት የአካታች ተከታች ግንኙነት ቃላትን በሚያዙት ፅንሰሃሣብ ስፋትና ጥበት መሰረት አካታች (ጠቅላይ) እና ተካታች (ዝርዝር) በሚል በሁለት ይከፈላሉ። አንዱ ቃል በርካታ ዝርዝር ጉዳዮችን አካቶ ሊይዝ ይችላል። ለምሣሌ “እንሰሳ” የሚለውን ቃል ብንወስድ በውስጡ ጅብ፣ ላም፣ ፈረስ፣ በግ፣ ዶሮ ወዘተ. በሙሉ አካቶ ይዟል። ስለዚህ እንደ “እንሰሳት” የመሳሰሉት ቃላት ጠቅላይ ናቸው ማለት ይቻላል። ምንውየለት(2005) Yule (1996፣119) ጠቅሰው እንደገለጹት የአንድ ቃል ፍች በሌላ ቃል ፍች የሚጠቃለል ሆኖ ከተገኘ የሁለቱ ቃላት ዝምድና የጠቅላይና ዝርዝር የፍች ግንኙነት ነው ማለት ይቻላል።

ከፍች አንፃር የቃላት ዝምድና የሚገለፅበት ሌላው መንገድ የቃላት ተዋረዳዊ ቁርኝት ነው፡፡ አንድ ቃል ሰፊ ያለ ፅንሰ ሀሳብ በመወከሉ የተነሳ በስሩ በርካታ ቃላት የሚኖራቸውን ፍች ሊያቅፉ ይችላሉ፡፡ ይህንን የአንድ ቃል ፍች በሌላው ቃል ፍች የሚጠቃለሉ ሆኖ ሲገኝ የሁለቱ ቃላት ዝምድና የአካታችነትና የተከታችነት የፍች ግንኙነትን ያመላክታል፤ በማለት ያስረዳሉ፡፡ እንደ Carter እና MacCarthy (1988፣26-27) ገለጻ ስለ የፍች ዝምድና በተመለከተ አካታችና ተከታች ቃላት የፍች ዝምድና አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ያለው የፍች ዝምድና የሚታየው በስሞች መካከል ነው ፤ ይሁን እንጂ ልክ እንደ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ትምህርት ፍችን መሠረት ያደረገ የቃላት ትምህርት ተደራጅቶ ከሚቀርብበት ስሌት አንዱ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው አካታች ተከታች ቃላትን ባንድ ላይ እያቀረቡ ተማሪዎች የቃላቱን የፍች ዝምድና እስከምን ድረስ እንደሆነ እንዲፈትሹ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይኸውም ተማሪዎች ጥቅል የሆነ ቃልን ሰጥቶ በስሩ ዝርዝር ወይም ነጠላ ቃላትን ተጠቅመው ጽሑፍ ወይም ንግግር እንዲያዘጋጁ የሚያደርጉና በሌሎችም ስልቶች ማከናወን ይችላል፡፡

### 2.3.2.2.3 የቃላት አብሮ ተሰላፊነት

የቃላት አብሮ ተሰላፊነት በአንድ ቋንቋ ቃላት መካከል መተሳሰርን የሚፈጥር ሌላው የዝምድና ማሳያ ነው፡፡ ምንውየለት (2005) የMaCarthy(1990) ጠቅሰው እንደገለጹት የቃላት አብሮ ተሰላፊነት ቃላትን ለመረዳት ሁለት ጠቃሚ የሆኑ ባህሪያትን እንዳለው ይጠቁማሉ፡፡ የመጀመሪያው የአንድ ቃል ባህሪ ይበልጥ አብሮት ከሚሰለፍ ቃል ጋር በመሆን ሰፋ ያለ ፍች እንደሚያስገኝ ማሳየት መቻሉ ነው፡፡ ይህም አብሮ ተሰላፊ ቃላቱን ለማስታወስ የሚረዳ ከመሆኑም በላይ የአንድ ቃል የፍች አካባቢን ለመለየት ያግዛል፡፡ ሌላኛው ባህሪው ደግሞ የትኞቹ ቃላት አንድ ላይ መገኘት እንደሚችሉ ተማሪዎች እንዲለዩ እና አብሮ ሊሰለፉ የሚችሉ ቃላት እንዲጠቀሙ ማስቻሉ ነው በማለት ይገልጹታል፡፡

ምንውየለት (2005) እንደገለጹት የቃላት አብሮ ተሰላፊነት ከፈሊጥ እና ከሌሎች ቃላዊ ሀረጋት አገላለፆች በተለየ በቃላት መካከል መተሳሰርን የሚፈጥር ነው፡፡ የቃላት አብሮ ተሰላፊነት በቃላት ጥናት ውስጥ ቃላትን አደራጅቶ ለማቅረብ ዋና መርህ በመሆን ያገግላል፡፡እንዲሁም የቃላት አብሮ ተሰላፊነት በቃላት አውዳዊ ፍች ላይ የሚመሰረት እና የሚተላለፍበት መንገድ ነው በማለት ምሁራንን በመጥቀስ ገልጸዋል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ከሞት ጋር መርዶ፣ ከደስታ ጋር የምስራች አብረው መሰለፋቸው የተለመደ ነው፡፡ ለሞት መርዶ ማለት እንደምንችል ሁሉ ለሞት የምስራች ማለት አንችልም፡፡ እንዲህ ያለውን የቃላት የአብሮ ተሰላፊነት ግንኙነት ለተማሪዎች ማቅረብ የትኛው ቃል ከየትኛው ቃል ቀድሞ ወይም ተከትሎ ይገባል የሚለውን እንዲለዩ ከማስቻሉም በላይ በተገቢው አውድ ተገቢውን ቃል መርጠው መጠቀም እንዲችሉ ያግዛቸዋል፡፡ የቃላት አብሮ ተሰላፊነትን ሊያሳዩ የሚችሉ መልመጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች ተጠቅሞ መቅረብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ይህም አንድን ቃል በአውድ ውስጥ በማቅረብ አብሮ የሚሰለፈውን ቁልፍ ቃል ቦታ ክፍት በማድረግ ተማሪዎቹ ቃሉን በክፍት ቦታው እንዲሞሉ በማድረግ፣ በዐረፍተ ነገራዊ አውድ ተገቢውን አብሮ ተሰላፊ ቃል በሌላ ቃል ተክቶ በማቅረብ ተማሪዎች ዐረፍተ ነገሩን በመመርመርና ተገቢ ያልሆነውን ቃል በመለየት በተገቢ ቃል እንዲተኩ በመጠየቅ ሊከናወን ይችላል፡፡

### 2.3.2.3 ቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ማቅረብ

ጌታሁን(1990) እንደሚገልጹት በአማርኛ ቋንቋ ቅጥያዎች ቃላትን የማርባትና የመመስረት ተግባር አላቸው፡፡ የእርባታ ሂደት የቃል መሠረታዊ ባህርይ ሳይለወጥ በቅጥያዎች አማካኝነት የሚደረግ የቃላት የእርባታ ይባላል፡፡ በቅጥያ አማካኝነት ከነበሩበት የቃል ክፍል ወደ ሌላ የቃል ክፍል የሚለዋወጡበት ሂደት ደግሞ ምስረታ ይባላል በማለት ያስረዳሉ፡፡ በተያያዘ Ur(1996) የቃላት ትምህርት እርባታናምስረታ ሂደታቸውን በመከተል የቃላት ማቅረብ የጎላ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ በቋንቋ ውስጥ በአንጻራዊ አነጋገር ጥቂት ቁጥር ያላቸውን የቃላት አፈጣጠር ሂደቶች በመከተል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አዳዲስ ቃላትን መፍጠር ይቻላል፡፡ ቃላት የተለያዩ አርቢ ምዕላዶችን ና በተለያዩ ሰዋሰዋዊ ባህሪያት ቅርፃቸውን ይለዋውጣሉ፡፡ በተያያዘም ባዬ (2000፣108-109) እንደሚገልጹት በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ቃላትን በማርባትና በመመስረት የሚያስችሉ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ቅጥያዎች አሉ፡፡ እነዚህ ቅጥያዎች በሰዋስዋዊ ተግባራቸው መሰረት በማድረግ የእርባታና የምስረታ ቅጥያዎች በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ የእርባታ ቅጥያዎች በቃል አምድ ላይ እየተቀጠሉ ቃልን በመደብ፣ በቁጥር፣ በሙያ፣ በእምርነት ወዘተ በማርባት የተለያዩ ቅርጽና ተጨማሪ ፍች እንዲኖራቸው ያደርጋሉ በማለት ይገልፃሉ፡፡

### 2.3.2.4 የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ

ተማሪዎች የአዳዲስ ቃላት ፍች ለመረዳት ፈጥነው መዝገበ ቃላትን ከማገላበጣቸው በፊት ቃላትን ከአገባባቸው እየገመቱ እና የቀደመ እውቀታቸውን እየተጠቀሙ ቢያነቡ ተመራጭነቱ አከራካሪ አይሆንም፡፡ሆኖም አንዳንድ ጊዜ የማያውቁትን ቃል ከአውዱ ለመገመት የሚያስችሉ ፍንጮች ላያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ ይህ ደሞ ከቋንቋ ክፍለ ጊዜ እጥረት እና ሌሎች ችግሮች ሳቢያ መምህራንን እንዲጠብቁ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ይህንን የጠባቂነት ችግር አስወግዶ በራስ የመተማመን ስሜት ከፍ ለማድረግ መዝገበ ቃላትን ተጠቅመው ፍችን እንዲያውቁ ማድረግ ጠቃሚ የማስተማሪያ ዘዴ ነው (Harmer 1991፣174,Gaims እና Redman1986፣76)፡፡

Summers(1988) በጥንቃቄ የተዘጋጀ መዝገበ ቃላት በውስጡ ከአንድ ቃል ጋር የፍች ዝምድና ያላቸው ቃላት የትኞቹ እንደሆኑ የቃሉ ድግግሞሽ፣ተዛማጅ ከሆኑ ሌሎች ቃላት ስርጭታቸው እና አጠቃቀማቸው እስከምን ድረስ እንደ ሆነ፣ከአንድ ቃል ጋር አዘውትረው የሚሰለፉ የትኛው ሊሆን እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡

### 2.3.2.5 ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ

Lewis(1993፣114) እንደሚገልጹት ተማሪዎች መግባባት እንዲቺሉ በተገቢ ሁኔታ በቃላት ትምህርት መታገዝ ይኖረባቸዋል በማለት ይገልጻሉ፡፡ በተያያዘ ቃላት ከሌሎች ክሂሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብ የመማር ሂደቱን የተቃና ያድረገዋል፡፡ ይህም ተማሪዎች የተግባቦት አቅም መጠኑን በጠበቀ የቃላት ትምህርት ክንውን እንዲታገዝ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች ቃላት የመረዳት ችሎታቸውን የሚያዳብሩት አቀባይ ክሂሎችን(መናገርና መጻፍ) ተጠቅመው ነው፡፡ ሌላው ተማሪዎች ቃላትን እንዲረዱ ከተፈለገ የቃላት ፍችን ግልፅ ለማድረግ ከሌሎች ቃላት ጋር አብረው እንዲያነቡ ወይም እንዲያደመጡ መደረግ አለበት፡፡ በአበዛኛው የቃላት ዕውቀት የሚጨበጠው በክሂሎች (በማዳመጥ ፣በመናገር ፣በማንበብ እና በመፃፍ) አጣምሮ መቅረብ ሲችል ነው፡፡ ተማሪዎች አዲስ ቃላት የያዙ ውህድ አሃዶችን ካነበቡ ወይም ካደመጡ በዋላ እንደገና እንዲናገሩ ውይም እንዲፅፉ ለማድረግ የሚያስችሉ መልመጃዎችን በጥናቃቄ በመቅረፅና በማቅረብ የቃላት ትምህርት ከክሂሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብ ይቻላል በማለት Eyraud (2000፣2) ያስረዳሉ፡፡

### 2.3.2.6 ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ማቅረብ

Grains (1986) ምንባብ አዳዲስ ቃላትን ለማስተማር የሚያስችል ጥሩ የማስተማሪያ ስልት ነው፡፡ በተለይ ጽሑፉ በተማሪዎች ዘንድ ተወዳጅነት ካለው ትምህርቱን እንዳይረሳ ስለሚያደርግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ስለዚህ መምህሩ ፅሑፉን ከመረጠ በኋላ በሚከተለው መልኩ ማቅረብ ይችላል፡-

- ቃላትን በምንባቡ መሠረት እና ከምንባቡ ውጭ ያላቸውን ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍች እንዲሰጡ በማድረግ

- ቃላትን በመስጠት በምንባቡ ውስጥ የእነዚህን ቃላት ተቃራኒ ወይም ተመሳሳይ ፍች የያዙ ቃላትን ከጽሑፉ ፈልገው እንዲያወጡ ማድረግ

- ከምንባቡ የወጡ ቃላትን በየቃል ክፍላቸው እንዲመድቡ በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይቻላል፡፡ በእርግጥ የሚቀርበው ፅሑፍ ለትምህርቱ ካለው ጠቀሜታ አንፃር ከተለያዩ አቅጣጫዎች ተመዝኖ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ከላይ ከተዘረዘሩት የማቅረቢያ ስልቶች ውስጥ ከተማሪዎች ደረጃ ፤ ከትምህርቱ ዓይነት ከጊዜው ኣንፃር በማጣጣም መምረጡ የመምህሩ ድርሻ ይሆናል በማለት ይገልጻሉ፡፡

### 2.3.2.7 የቃላት ትምህርቱን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ

የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ተቀርጸውለት ለተማሪዎች ሲቀርብ ለመለማመድ እንዲያስችላቸው ግልፅ ሆኖ በተብራራ ሁኔታ የሰፈረ መመሪያ ሊኖረው ይገባል Alderson (1995፣41)፡፡ ስለቃላት ትምህርት መመሪያዎች በተመለከተ Wallace(1988፣73) እንደሚገልጹት ግልፅ ማብራሪያ የታከለባቸው የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ለማዘጋጀት በቃላት ትምህርት ላይ ያተኮሩ ምርምሮችን መቃኘት አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ ተመሳሳይ ቃላትን ለማለማመድ የተዘጋጁ መልመጃዎች ቢኖሩ የተመሳሳይ ቃላቱ ፍካሬያዊና እማሬዊ ፍቺያቸው ፣ ከሚገቡበት አውድ ወይም አብረው ሊሰለፉ ከሚችሉ ሌሎች ቃላት አንፃር ሊመዘኑ ይገባል ምክንያቱም ተመሳሳይ ቃላት አጠቃላይ በሆነ እይታ ተመሳሳይ ቢመስሉም በተግባር ሲመረመሩ ግን ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚችል ይታመናል፡፡ ስለዚህ የተመሳሳይ ቃላት ትምህርት የሚቀርብባቸው መመሪያዎች ይህንኑ መመሳሰል አንፃራዊ መሆኑን የሚጠቁም ማብራሪያ ቢታክልባቸው ተማሪዎቹ የቀረቡላቸውን መልመጃዎች በተፈለገው

መንገድ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ግልፅና የተብራሩ፣ አስፈላጊውን ምሳሌ የያዙ ሊሆኑ ይገባል፡፡

### 2.3.2.8 ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ

Scrivemer (1998፣75) እንደሚገልጹት የቃላት ትምህርት ትኩረት ነጠላ የሆኑ ቃላትን ብቻ ሳይሆን ረጅምና ባለብዙ ሀረጎችንም ማተት አለበት፡፡ በተያያዘ Lewis (1993፣98) የቃላት ትምህርት ቃላዊ ሀረጋትን በቃላት ትምህርት ውስጥ ማካተት ከቻለ ተማሪዎች በቋንቋው በሚገባ ለመግባባት እንዲችሉ ከማገዝ አንፃር ትልቅ ድርሻ አለው ፡፡ ቃላዊ ሀረጎችን በቃላት ትምህርቱ ማካተትና ማቅረብ ተማሪዎች በሚያጋጥማቸው የተግባቦት አውድ አንደበተ ርቱዕ ሆነው አላማቸውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችላቸውን መሳሪያ ያስታጥቃቸዋል በማለት ያስረዳሉ፡፡ Nattinger(1988) እንደሚገልጹት ብዙ የቋንቋ ብቃት ትዎራዎች የሚጠቁሙት ቃላት በትውስታ ማህደር የሚቀመጡት ነጠላ ሆነው ብቻ ሳይሆን የሀረግ አካል ሆነው ጭምር እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ እነዚህ ቃላዊ ሀረጎች በቀላሉ ሊታወሱ ከመቻላቸውም በላይ ተናጋሪው በነጠላ ቃል ላይ እንዳያተኩርና ሃሳቡን በዲስኩር መዋቅር ላይ እንዲያሳርፉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ፡፡

### 2.4 የመማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያዎች ለቃላት ትምህርት አተገባበር ያላቸው ሚና

Richard (1990) መርሐ ትምህርት የተለያዩ የትምህርት አይነቶችን ለማቀድ እንደመሠረት ሆኖ የሚያገለግል የይዘቶች ሀተታ ነው፤እንዲሁም ቋንቋን በመማር ማሥተማር ረገድ መምህራንና ተማሪዎች ግባቸውን ለማሣካት የሚመሩበት መማሪያ መንገድ ነው፡፡ ፍላጎት ለመለየት፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመምረጥ፣ የመማሪያ መፃህፍት ለማዘጋጀት፣ የይዘት መረጣ፣ ቅደም ተከተሉንና ወሰኑን ለመለየት፣ የትግበራ እቅዱን በቅደም ተከተል ለማዘጋጀት፣ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎችእና አላማን ለማስቀመጥ የመርሃ ትምህርት ወሳኝ አካላት ናቸው በማለት ይገልጻሉ፡፡ በልስቲ (2013) በጥናቷ የYalden (1987)፣ Dubin እና Olishtain(1986) እና Ur (1996) ጠቅሰው እንደገለጹት፣ መርሃ ትምህርት በውሥጡ የትምህርቱን አይነት አስመልክቶ የሚቀርቡትን አላማዎች፣ ይዘቶች፣ መረጃ መሣሪያዎችና የምዘና ሥልቶችን በማካተት ሥርዓት ባለው መንገድ ተቀነባብሮ የሚቀርብእና ለመማር ማሥተማሩ የተዘጋጀ የትምህርት ፕሮግራም ነው፡፡ በተጨማሪም ታላሚው አካል ወይም ተማሪው ከአካባቢው የሚያገኘውን የሕይወት ልምድና እውቀት በመጠቀም የባሕርይ ለውጥ

እንዲያመጣ በተወሠነ ቦታና ጊዜ የሚሠራበት የትምህርት እቅድ ነው፡፡ በዚህም ስለቃላት ትምህርት አተገባበር የሚሆኑትን የይዘት ዓይነት መጥኖ በማቅረብ፣የሚቀርቡት ዘዴዎችን እና መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቆም ረገድ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል በማለት ይገላፃሉ፡፡

በተያያዘ በልስቲ (2013) Yalden (1987) በመጥቀስ እንደገለጹት መርሐ ትምህርት መምህራን እና ተማሪዎች የሚያሳኳቸውን ግቦች በማቅረብ እንደ መመሪያ የሚያገለግል፣ተማሪዎች የሚማሩትን ይዘት ማጠቃለያ አድርጎ ሊወሰድ የሚችል እና ለትምህርት የሚቀርቡ ይዘቶችን የሚዘረዝር ነው:: መርሐ ትምህርት መምህሩ የአንድ ትምህርት አይነት ርዕሰ ጉዳዮችን እና ተማሪዎች የሚማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች የሚያስተምረውን ትምህርት ለማዘጋጀት የሚጠቀምበት መሳሪያ ነው በማለት ይገልጹታል፡፡

ብሩክታዊት(2001) የGains(1986:172) ጠቅሰው እንደገለጹት፣ ስለ መምህሩ መምሪያ አስፈላጊት ሲገልጹ የመምህሩ መሪ መጽሐፍ ለመምህሩ የትምህርቱ ምን አይነት አካሄድ መከተል እንዳለበት ዝርዝር ሃሳብ በመስጠት አቅጣጫ የሚጠቁም አስፈላጊ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ የመምህሩ መሪ መጽሐፍ አንዱ የማስተማሪያ ግብአት ሲሆን የቃላት ትምህርት በምን መልኩ መቅረብ እንዳለበት እና በምን አይነት የመርጃ መሣሪያ መደገፍ እንዳለበት የሚጠቁም መሣሪያ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የትኛውንም ዕውቀት ለማስጨበጥ የሚስጡት ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ አንድ ተጓዥ ወደ ማይታወቅ አቅጣጫ ሲሄድ ሲያቅድ የአካባቢውን አቀማመጥ የሚያሳይ ካርታ እንደሚስፈልገው ሁሉ መምህራንም የትምህርት አቅጣጫውን የሚመራቸው መማሪያ መጽሐፍት መጠቀም እንዳለባቸው ያብራራሉ፡፡ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ለተማሪ ከሚሰጡት ጥቅም በተጨማሪ ለቋንቋው አስተማሪዎች የሚሠጡት ጥቅም ከፍተኛ ነው በማለት ያብራረሩ፡፡

Richards (2001፣251) ይህንን አስመልክተው ሲገልጹ በተለይም ለአዲስ እና ጀማሪ መምህራን የተሻለ የማስተማሪያ ዘዴ አቅጣጫዎች በመጠቆምና የት ላይ ማተኮር እንደለባቸው በመምራትና የማስተማሩን ስራ የተቃና በማድረግ ረገድ የመምህሩ መሪ መጽሐፍት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው በማለት ይገልጻሉ፡፡

እነዚህ እስካሁን የተገለጹት የመማሪያ ማስተማሪ መሣሪያዎች የትምርቱን አላማ ወደ ተግባር ለመለወጥ ወሳኝ ናቸው፡፡ መርሐ ትምህርቱን መሠረት ያደረጉ መማሪያ ማተማሪያ መጽሐፍት

ለቋንቋ ትምህርት በመምህራን አማካኝነት ግልፅና ተጨባጭ ሆኖ ለተማሪው እንዲደርስ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

## 2.5 በቃላት ትምህርት አቀራረብ ና አተገባበር ላይ የሚያጋጥሙ ተለዋዋጮች

ደረበ (1994) Edcutiona and Training Police (ETP) በመጥቀስ እንደገለጹት የመፅሐፍ እጥረት፣በክፍል ውስጥ የሚገኑ የተማሪ ቁጥር ብዛት፣የማስተማሪያ ግብኣቶች ያለማሟላት፣ለመምህራን በቂ የሆነ ስልጠናዎች ያለመኖር ለትምህርት ጥራት መውደቅ ከፍተኛ ምክንያቶች እንደሆኑ በመጥቀስ እነዚህ ችግሮች በቃላት ትምህርት ሂደት ውስጥ ያላቸው ተፅኖ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ይገልፀሉ፡፡

በቃላት ትምህርት አቀራረብና አተገባበር ላይ የሚያጋጥሙ ተፅዕኖዎች በተመለከተ ደረበ(1994) የWest(1963) በመጥቀስ እንደገለጹት ችግሮቹን ከመምህራን፣ከተማሪና ከማስተማሪያ ግብኣቶች አንፃር በማለት ጠቅሷቸዋል፡፡ ከመምህርን አንፃር የሚታዩ ችግሮች የአቅም ችግር፣ፍልጎት ያለመኖር(አመለካከት ችግር)እና የክፍለ ጊዜ መደራረብ የሚሉት ናቸው፡፡ከተማሪ አንፃር የአመለካከት ችግር እና የተማሪ ቁጥር ብዛት እንዲሁም የማስተማሪያ ግብአቶች ያለማሟላት በቃላት ትምህርት አቀራረብናአተገባበር ላይ የሚጋጥሙ ችግሮች መሆናቸው ይጠቀሳሉ፡፡

## 2.6 የተዛማጅ ፅሑፍ ቅኝት

ቃላትን ትምህርት በተመለከተ ከተሰሩ ጥናቶች መካከል አንዱ የብሩክታዊት ተስፋዬ (2001) በመቀሌ ከተማ በሚገኙ ለሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የቃላት ትምህርት አተገባበር ፍተሻ በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት ሲሆን አላማው በመቀሌ ከተማ በሚገኙ ፍሬ አብዮት፣ አይደርና ወልደ ንጉስ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ከዘመናዊ የቃላት ትምህርት አመለካከት አንጻር በምን አይነት ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መመርመር ነው፡፡ አይነታዊ እና አሃዛዊ የአጠናን ዘዴ ተከትሎ በገለጻ አቀራረብ የቀረበ ሲሆን መምህርን የቃላት ትምህርት በአብላጫ የሚጠቀሙትን ዘዴዎች፣ የመርሃ ትምህርቱ የመማሪያ መምሪያ ለክፍል ውስጥ ያላቸው አስተዋጽኦ እና በቃላት ትምህርት አተገባበር መምህራን የሚያጋጥማቸው ችግሮች ለይቷል፡፡ መርዓ ትምህርት ለቃላት ትምህርት የሠጠው ክፍለ ጊዜ ጥሩ መሆኑ፣ መምህራን ቃላትን ሲያስተምሩ ምን ችግር እንደሚያጋጥማቸው፣ መርሃ ትምህርቱ ቃላትን የማስተማሪያ መረጃ መሳሪ በተወሰነ መልኩ እንደሚጠቁም በአዛምድ፣ በምንባብ ፣ በተመሳስሎና በተቃራኒ የሚቀርቡ ቃላት ከፍተኛ

ደረጃ መያዛቸው በጥናቱ ማጠቃለያ ግኝት ላይ አብራርቷል፡፡ በተጨማሪ ለቃላት ትምህርት አተገባበር ላይ ችግር ናቸው ብሎ የዘረዘራቸው ሀሳቦች መሰረት በማድረግ የመፍትሔ ሀሳቦችን ሰንዝራል፡፡የብሩክታዊት ጥናት የቃላት ትምህርት አተገባበር ላይ ብቻ ማተኮሩ እና በሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናቱ መካሄዱ ይህ ጥናት ደግሞ የቃላት አተገባበር በተጨማሪ አቀራረብ ላይ ማተኮሩ እና በአንድ ትምህርት ቤት የሚካሄዱ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ሲለያይ የቃላት ትምህርት አተገባበር ላይ ማተኮሩ ያመሳስላቸዋል፡፡

የደረበ ሙሉ (1999) በትግረኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቃላት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ በሚል ርዕስ የተደረገ ጥናት ሲሆን አላማውም በትግራይ ክልል ሰሜን ምዕራብ በሚገኙ የሽሬ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤት፣የሐክፊን ሁለተኛደረጃ ትምህርት ቤት ፣ የእንዳባጎና ከፍተኛ ሁለተኛ ትምህርትቤት እና የአዲዳሮ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት ትምህርት እንዴት እንደሚያቀርቡ መፈተሽ ነው፡፡ የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ስልቶችን ከመጠቀም አንጻር የተወሰኑ መምህራን እንደሚጠሟቸው አንዳንዶችን ደግሞ ዝቅተኛ ትኩረት እንዲሚሰጧቸው በጥናቱ ውጤት ገልጿል፡፡ የደረበጥናት መምህራን ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጉ እና በሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናቱ ማካሄዱ ይህ ጥናት ደግሞ ከመምህራን በተጨማሪ ተማሪዎች ላይም ትኩረት ማድረጉ እና በአንድ ትምህርት ቤት ላይ ጥናት የሚያደርግ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ሲለያይ በቃላት ትምህርት አቀርረብ ላይ ማተኮሩ ጥናቱ የሚካሄው በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ማተኮሩ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

ጌታሁን አያና (2011) ዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የቃላት ትምህርት ይዘት አቀራረብ ግምገማ በሚል የቀረበ ጥናት ሲሆን የዚህ ጥናት ዓላማ በሀገር አቀፍ ደረጃ የዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍት የቃላት ትምህርት ይዘት አቀራረብ ቃላትን ከማስተማር አኳያ ያላቸውን ብቃት መፈተሽ ነው፡፡አጥኚው በመማሪያ መፅሐፍቱ ላይ የሠነድ ፍተሻ ማድረግና እና በአጋዥነትም አማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማስተማር ብዙ ልምድ ያላቸውን መምህራን ቃለ መጠይቅ በማድረግ በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል፡፡በሁለቱም መማሪያ መፅሐፍች የጥምር ቃላት በመረዳትና አፈልቆ በመጠቀም በሚያስችል መልኩ አለመቅረባቸውን፣ የቃላት ትምህርቱ በተለይ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከማዳመጥ ክሂል ጋር

እንዲሁም አስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከንግግርና ከማዳመጥ ክሂል ጋር ተጣምረው አለመቅረባቸውንና የመዝገበ ቃላትን አጠቃቀም ጥበብ እንዲያውቁ የሚያግዙ መልመጃዎች በጥራትና በበቂ መጠን አለመካተታቸውን ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ በመጨረሻም ጥናቱ የመማሪያ መጽሀፍቹ የቃላት ትምህርት ይዘት አቀራረብ ችግሮችን ለመቅረፍ ያስችላሉ ያላቸውን አስተያየቶች ሰንዝሯል፡፡ይህ ጥናት በሀገር አቀፍ ደረጃ የዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍት የቃላት ትምህርት ይዘት አቀራረብ ቃላትን ከማስተማር አኳያ ያላቸውን ብቃት መፈተሽ በሚል መማርያ መፅሐፉ ላይ ማተኮሩ እና የዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል ሁለቱንም የክፍል ደረጃ መማርያ መፅሐፍቶች ላይ አካላይ ማድረጉ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ የቃላት ትምህርት አቀራረብና አተገባበር ላይ መምህራንንና ተማሪዎች ላይ ማተኮሩ ሲለያያሉ የቃላት ትምህርት ይዘት አቅራረብ መዳሰሱ ጥናቶቹ ያመሳስላቸዋል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ንድፍ እና መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

### 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል የቃላት ትምህርት አተገባበር ትንተና ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ ጥናት መሰረት የሚያደርገው ዓይነታዊ ምርምር (Qualitative Research) እና አሃዛዊ የምርምር ዘዴን (Qantitative Research) የሚከተል ነው፡፡ ይህ ጥናት ዓይነታዊ ምርምር መረጃዎቹን በፅሁፍ መጠይቅ እና በምልከታ የሚሰበሰበው መረጃዎችን በዝርዝር እና በፐርሰንት ትረካዊ ወይም ገላጭ መንገድን በመከተል ትንተናው ሲያቀርብ እስታስቲካዊ መረጃዎችን አሃዛዊ የምርምር ዘዴ ተጠቅሞ አቅርቧል፡፡

### 3.2 የመረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የቃላት ትምህርት  አተገባበር ትንተና በሚል አላማ ርዕስ የቀረበ ሲሆን ለጥናቱ የመረጃ ምንጮቹ ሆነው ያገለገሉት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡

### 3.3 የናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት በጉራጌ ዞን በቡታጀራ ከተማ ከሚገኙ ሁለት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ትምህርት  አተገባበር ይመለከታል፡፡ በመረጃ ምንጭነት የሚያገለግሉት ናሙናዎች ለመምረጥ የተለያዩ የናሙና አወሳሰድ ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ ተጠኚ ተደርገው የተመረጡ የዘጠነኛ ክፍል መምህራን እና ተማሪዎች ናቸው፡፡

#### 3.3.1 የጥናቱ ክልል ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው ክልል የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ሲሆን የተመረጠው በአመቺ ናሙና ዘዴ ነው፡፡ በአመቺ ናሙና የተመረጠበት ምክንያት አጥኚው በክልሉ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ያስተማረ አካባቢውን የሚያውቅ፤ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሊያገኝ የሚችል እና በተጨማሪ አጥኝው በዚህው ክልል በስራ ላይ እያለ የሚያጠናው በመሆኑ ሌላ

ክልል ሄዶ የማጥናት ከጊዜው አንፃር ስለማይችል ጥናቱን  በስራ ገበታ ላይ  ያለበትን ክልሉን መርጣል፡፡

### 3.3.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የሚከናወነው በጉራጌ ዞን በቡታጀራ ከተማ ከሚገኙ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ነው፡፡ ትምህርት ቤቱም የተመረጠው በአመቺ የናሙና አወሳሰድ ስልት ነው፡፡ ጥናቱ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወስጥ ቢጠና የተሻለ ይሆናል ብሎ አጥኚው ያመነበት ምክንያት፤ የአጥኚው የስራ ቦታ አቅራቢያ በመሆኑ ጥናቱን በቅርበት ለመከታተል፤ በጥናቱ የሚሳተፉ መምህራንና ተማሪዎችን መረጃ የመስጠት ትብብር ለማግኘት በማሰብ እና  በቅርበት መገኘቱ በህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን መርጧል፡፡

### 3.3.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናታ ውስጥ ተጠኚ ተድርገው የተመረጡ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡት በይሁነኝ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ነው፡፡ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አዲስ በመሆናቸው እና ለአማርኛ ቋንቋ ትምህር የሚሰጡት አመለካከት በአንጻሩ ከሌሎቹ በጣም የተሻለ በመሆኑ፤ አጥኚው አስረኛ ክፍል እያስተማረ ስለነበር ለጥናቱ ስለማይመች እና የአስራአንድና የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በአገር አቀፍ ፈተና ስለማይሰጥ እንዲሁም ለአማርኛ ቋንቋ ትምህር ትኩረት እንደማይሰጡት አጥኚው በመገንዘቡ ጥናቱ ውስጥ ቢካተቱ ትክክለኛውን መረጃ ማግኘት ያዳግታል በሚል የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ መርጣል፡፡

### 3.3.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት በጉራጌ ዞን በቡታጀራ ከተማ ከሚገኙ ሁለት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቃላት ትምህርት  አተገባበር ትንተና ይመለከታል፡፡ በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሁለት ሴትና አንድ ወንድ በድምሩ ሶስት ሲሆኑ የቃላት ትምህርት አተገባበራቸው ምን ይመስላል? የሚለውን ለማወቅ ሶስቱም በጠቅላይ ንሞና ዘዴ በዚህ ጥናት ስር ተካተዋል፡፡ ሶስቱም

መምህራን በጥናቱ የተካተቱበት ምክንያት የተለያዩ የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶችን እንደሚጠቀሙ እና አቀራረባቸውና አተገባበራቸው ልዩነት ለመፈተሽ ሲባል ሶስቱም በጥናቱ ስር ተካተዋል፡፡

በዚህም መሰረት መምህራን ለጥናቱ በመረጃ መሰባሰቢያነት ከሚያገለግሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መካከል የፅሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፤ በተጨማሪ በፅሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የክፍል ውስጥ ምልከታ ተደርጓል፡፡

***ሠንጠረዥ 1፡- በመረጃ ሰጭነት የተሳተፉ መምህራን ዝርዝር መረጃ***

| ት/ቤት | የመጀመሪያ ዲግሪ | | | ሁለተኛ ዲግሪ | | | ጠቅላላ ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| በህር ሀለተኛ ደረጃ ት/ቤት | - | 2 | 2 | 1 | - | 1 | 1 | 2 | 3 |

### 3.3.5 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነትምህርት በመማር ላይ ከሚገኙት ዘጠኝ የዘጠነኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎች መካከል ሶስት የመማሪያ ክፍል ተማሪዎች በቀላል እጣ ናሙና (Simple Random Sampling) ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ከላይ የመምህራን አመራረጥ ላይ እንደተገለጸው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሶስት ሲሆኑ ሶስቱም እያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት ክፍሎችን የሚስተምሩ ሲሆን በሚያስተምሩበት ክፍል ለእያንዳዳቸው አንድ የዘጠነኛ መማሪያ ክፍል በአመቺ ናሙና በመረጃ ሰጭነት ተወስዷል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት መምህራን የቃላት ትምህርት አተገባበራቸው ምን ይመስላል? የሚለውን ለማወቅ በሚያስተምሩበት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በወካይ ናሙናነት መመረጥ ስላለበት በእያንዳንዱ ክፍል ላሉ ተማሪዎች በነሲብ ዕጣ ናሙና አመራረጥ መሰረት የተማሪዎች ስም ዝርዝር በማዘጋጀት ዕጣ እንዲያወጡ በማድረግ በእያንዳንዱ ክፍል 35 ተማሪዎች ከሶስቱ የመማሪያ ክፍሎች በአጠቃላይ 105 ተማሪዎችን በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ ከዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በእጣ፣ በአመቺ ናሙና ዘዴ ተመርጦ በጥናቱ ተሳታፊ ተደርጓል፡፡

የፅሑፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ከተመረጡ ተማሪዎች 3ቱ በትክክል ያልሞሉ ወይም የአሞላል ችግር ያለባቸው 6 ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ያልተገኙ በድምሩ 9 ተተኳሪ ተማሪዎች ከጥናቱ ውጭ ሆነዋል፡፡ በመሆኑም 96 ተማሪዎች ብቻ የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

### 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

አንድ ጥናት ወደ ግብ የሚደርሰው ትክክለኛ መረጃዎች በመሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት በመሰበሰብ እና በመተንተን ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጉራጌ ዞን በቡታጀራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል መምህራን ተተካሪ ያደረገ የቃላት ትምህርት አተገባበር ትንተና ሲሆን አጥኚው ለዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት የፅሑፍ መጠይቅ እና ምልከታ ተጠቅሟል፡፡ በፅሑፍ መጠይቅ መረጃዎችን በመሰብሰብ ፤ ክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት ክትትል ምልከታ በማድረግ መረጃዎችን አረጋግጧል፡፡

#### 3.4.1 ምልከታ

በዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ተግባራዊ ከተደረጉት መካከል ምልከታ አንዱ ነው፤ምክንያቱም የጥናቱ አላማ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ትምህርት አተገባበር ትንተና ሲሆን ይህና አላማ በአግባቡ ለማሳካት ይችል ዘንድ በዋናነት በመረጃ መሰብሰብያ የተመረጠው ዘዴ ምልከታ ነው፡፡

የክፍል ውስጥ ምልከታ በቋንቋ ትምህርት ክንውን ወቅት የመምህሩ ብቃትና አቀራረብ ያሳያል፡፡ መምህራን በክፍል ውስጥ ቃላትን ሲያስተምሩ አተገባበራቸው ምን ይመስላል? የሚለውን የምልከታ መከታተያ ቅፅ አጥኝው በማዘጋጀት መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ ስለዚህ ለዚህ ጥናት የቃላት ትምህርት አተገባበር በተመለከተ ሶስት መስፈርቶች እና አስራ አምስት የምልከታ መከታታያ ጥያቂ ቅፅ አዘጋጅቷል፡፡ በጥናቱ አማካሪ እና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ ሁለት መምህራን ታይቶ አስተያየት ከተሠጠው በኋላ ተስተካክሎ መረጃዎችን ተሰብስቦበታል፡፡

የተገኘውን መረጃ ከንድፈ ሀሳብ ክለሳ ጋር በማቀናጀት ለጥናታዊ ጽሑፍ ግብዓት ለመስጠት ጠቀሜታው የጎላ ስለሆነ ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪነት ተጠቅሟል፡፡ ስለሆነም ከሶስቱም ተተኳሪ መምህራን ከሚያስተምሩት ሶስት መማሪያ ክፍሎች በእጣ ናሙና አመራረጥ ስልት የተመረጡ ሲሆን አጥኚውናተጠኚ መምህራን ምልከታ የሚካሄድበት የጊዜ ሰሌዳ

በስምምነት በማውጣት ለእያንዳንዳቸው ተጠኚ መምህራን ሶስት ሶስት ጊዜ  አጥኚው ምልክት አካሂዷል፡፡ ምልከታውን ለማከናወንም ሰባት ሳምንታት ወስዷል፡፡

### 3.4.2 የፅሑፍ መጠይቅ

የፅሑፍ መጠይቅ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያዎች መካከል መላሾቹ አስተማማኝ መረጃ እንዲሰጡ ያበረታታል፤ ጊዜንና ጉልበትን ይቆጥባል፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናት በፅሑፍ መጠይቅ በመረጃ ሰጪነት ከተመረጡት የዘጠነኛ ክፍል መምህራ እና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ስለቃላት ትምህርት አተገባበር በተመለከተ ለመምህራን አስራ ስምንት የፅሑፍ መጠይቆች እንዲሁም ለተማሪዎች አስራ አራት የፅሑፍ መጠይቆች አዘጋጅቶ ጠይቋል፡፡ ለመምህራን የተዘጋጁ የፅሑፍ መጠይቆቹ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ስለ መምህሩ የግል ሁኔታ የሚጠይቁ፣ስለቃላት ትምህርት የማስተማርያ መንገዶች የሚመለከት በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ የሚሉ መልሶች የሚሹ በሠንጠረዥ የቀረቡ ጥያቄዎች እንዲሁም መምህሩ ስለ ቃላት ትምህርት አተገባበር የግሉን አስተያየት የሚያንፀባርቅበት ጥያቄዎች ናቸው፡፡

ለተማሪዎች የቀረበው የፅሑፍ መጠይቅ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን መጠይቁን ስለ ተማሪው መረጃ የሚገልፅ ፤ ስለቃላት ትምህርት አተገባበር በተመለከተ በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ የሚሉ መልሶች የሚሹ በሠንጠረዥ የቀረቡ ጥያቄዎች እና ለተማሪዎች ስለቃላት ትምህርት፡፡ አተገባበር በተመለከተ የግል አስተያት የሚያንፀባርቁበት ጥያቄዎች ናቸው፡፡

እነዚህ የፅሑፍ መጠይቆች ልክ እንደ ምልከታው በጥናቱ አማካሪ እና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ  ሁለት መምህራን አስተያየት ተሰጥቶባቸውና ተስተካክለው ስራ ላይ የዋሉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ አጥኚው መረጃው ከመሰብሰቡ በፊት ስለ ጽሑፍ መጠይቆቹ አላማ ለመምህራንና ለተማሪዎች ገለፃ በማድረግ መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡

## 3.5. የመረጃ አተናተን

ለዚህ ጥናት አጥኚው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ከሚባሉት መካከል በጽሑፍ መጠይቅ እና በምልከታ መረጃዎችን በመሰብሰብ በስርዓት አደራጅቷል፡፡ በሶስት ምልከታ መከታተያ ቅፅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ወደአንድ የምልከታ መከታተያው ቅፅ በማስፈር የምልከታ መከታተያ ቅፅ

መስፈርቶች መሰረት በማድረግ የቀረቡ በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ በሚል የተሰበሰቡ መረጃዎች በቁጥር በሰንጠረዥ ሰፍረው በተጨማሪ በሰንጠረዥ የቀረቡ መረጃዎች ተተንትነው ቀርቧል፡፡

ለመምህራን በፅሑፍ መጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ በሚሉ መልሶች የተሰበሰቡ መረጃዎች በአሃዝና በሰንጠረዥ ሰፍረው በተጨማሪ በሰንጠረዥ የቀረቡ መረጃዎች ተተንትነው ቀርቧል፡፡ ለተማሪዎች በፅሑፍ መጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ በሚሉ መልሶች የተሰበሰቡ መረጃዎች በቁጥር በመቶኛ እና በሰንጠረዥ የቀረቡ ሲሆን በተጨማሪ በሰንጠረዥ የቀረቡ መረጃዎች ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

ይህ ጥናት አላማው በጉራጌ ዞን በቡታጀራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪ ያደረገ የቃላት ትምህርት አተገባበር ትንተና ሲሆን በዚህ አብይ አላማ ስር ጥናቱ ያነሳቸው ጥያቄዎች መምህራን የትኛውን የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶችን ይበልጥ ይጠቀማሉ እና የክፍል ውስጥ የአተገባበር ሂደት ምን ይመስላል በተጨማሪ ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ያላቸው ተሳትፎ ምን ያህል ነው? የሚሉትን ጥያቄዎችን ለመመለስ ለመምህራንና ለተማሪዎች በፅሑፍ መጠይቆች እና በክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች በመተንተን ከላይ የቀረበው የአብይ አላማ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

### 4.1 የመረጃዎች ውጤት ትንተና

የቃላት እውቀት ሲባል ቃላትን መረዳትና የተረዱትን ወይም ያወቁትን ቃላት በሚፈለገው ጊዜና ቦታ አውጥቶ መጠቀም መቻልን ይመለክታል በማለት ምሁራን ይገልፃሉ:: ስለሆነም ተማሪዎች አስገላጊውንና ተገቢውን ቃል መረዳት ወይም መጠቀም እንዲችሉ ምን አይነት የቃላት ይዘቶችን ማስተማር አለብን? የሚለውን ጥያቄ መልስ ሊኖረው ይገባል፡፡ እንደ Harmer(1991) እና Ur (1996) ገለፃ ተማሪዎች ሊያውቋቸው የሚገቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላት ቅርፅ፣የቃላት አገባባ፣ የቃላት አጠቃቀምና የቃላት ትርጉም በማለት ይገልፃሉ፡፡

በዚህ ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች በተመለከተ የመምህራን አቀራረብና አተገባበር ማሳየት ነው፡፡ በተጨማሪ በቃላት ትምህርት የተማሪዎች ተሳጥፎንም ተመልክቷል፡፡ በምልከታ እና ለመምህራንና ለተማሪዎች በቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ መሰረት በማድረግ ተደራጅተው ቀርቧል፡፡

ከላይ የቀረቡ ሃሳቦች እንደሚጠቁመው በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበቡ መረጃዎች በዚህ ክፍል ተተንትኗል፡፡ በምልከታ የተገኙ የቃላት ትምህርት አተገባበር የተመለከቱ መረጃዎች፤የቃላት ትምህርት አቀራረብ በተመለከተ በምልከታእና በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ

መረጃዎች በተጨማሪ የመምህራንና የተማሪዎች ስለቃላት ተጨማሪ አስተያየቶችን በቅንጅት ቀርቧል፡፡

## 4.2 የቃላት ትምህርት ማስተማሪያ መርሖች በተመለከተ

ሠንጠረዥ 2፡ *የቃላት ትምህርት ማስተማሪያ መርሖች በተመለከተ በተደረገ ምልከታ የተገኘ መረጃ*

| ተ.ቁ | የምልከታ መስፈርቶች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቃላት ትምህርት ማስተማርያ መርሖች በተመለከተ | | | | | |
| 1.1 | ዓላማን ስለመያዝ | | | | 2 | 1 |
| 1.2 | የሚቀርቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከክፍለ ጊዜው እና ከተማሪዎች ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ | | 1 | 2 | | |
| 1.3 | የቃላትን ትምህርት ለትውስታ በሚመች መልኩ ስለማስተማሩ | | 1 | 1 | 1 | |
| 1.4 | ሁኔታዊ አቀራረብ ስለመከተሉ | | 1 | 2 | | |
| 1.5 | ቃላትን ለትንበያ በሚመች መልኩ ስለማቅረቡ | | 1 | 2 | | |
| 1.6 | ቃላትን አቧድኖ ስለማቅረቡ | | | 1 | 2 | |

ከላይ ከመከታታያው ቅፅ እንደሚጠቁመው በዚህ ጥናት የቃላት ትምህርት የማስተማሪያ መርሖች መካከል መምህሩ ለምን እንደሚያስተምር ዓላማ ሊኖረው ይገባል፤በዚህም መሰረት ከምልከታው የተገኘው መረጃ ሁለት መምህራን (66.66) ከፍተኛ እና አንድ መምህር (33.33) በጣም ከፍተኛ መካከለኛ በሆነ መልኩ ለምን እንደሚያስተምሩ አላማን መሰረት ያደረጉ ሆነው ታይቷል፡፡ የቀረቡ የቃላት ትምህርት ይዘት እና ከክፍለ ጊዜው እንዲሁም ከተማሪዎች ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ በተደረገ ምልከታ አንድ መምህር(33.33) ዝቅተኛና ሁለት መምህራን (66.66) መካከለኛ በሆነ መልኩ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

የቃላትን ትምህርት ለትውስታ በሚመች መልኩ ከማስተማር አንፃር አንድ መምህር (33.33)ከፍተኛ፣አንድ መምህር (33.33) መካከለኛ እንዲሁም አንድ መምህር (33.33) በዝቅተኛ ደረጃ ሲያስተምሩ ታይቷል፡፡ ሁኔታዊ አቀራረብ ተከትሎ ከማስተማር አንፃር አንድ መምህር (33.33) ዝቅተኛ ሁለት መምህራን (66.66)መካከለኛ በሆነ መልኩ ሲያስተምሩ ታይቷል፡፡ መምህራን ተማሪዎቻቸው የቃላት ችሎታቸውን በራሳቸው ጥረት እንዲያሳድጉና እንዲማሩ በዐውድ ውስጥ ቃላት እንዴት ፍችቻቸውን መተንበይ እንዳለባቸው ማለማመድ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር ቃላትን ለትንበያ በሚመች መልኩ ከማቅረብ አንፃር አንድ መምህር(33.33) ዝቅተኛ፣ሁለት መምህራን (66.66) በመካከለኛ ደረጃ ሲያስተምሩ ታይቷል፡፡ ቃላትን በተመሳሳይ ባህሪያቸው፣ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ፣በሚኖራቸው የፍች ተዛማዶ እና በፍች ተቃርኖ ማቧደን ይቻላል፤በዚህም ቃላትን አቧድኖ ከማቅረብ አንፃር ሁለት መምህራን (66.66) ከፍተኛ እና አንድ መምህር (33.33) በመካከለኛ በሆነ ደረጃ ሲያስተምር ታይቷል፡፡

### 4.3 የቃላት ትምህርት ማስተማሪያ መንገዶች በተመለከተ

#### 4.3.1 ቃላትን በአውድ ማስተማር

የቃላት ትክክለኛ ፍች የሚታወቀው ቢያንስ ቃሉ በአረፍተ ነገር አወድ ውስጥ ሲገባ እንደሆነ Wallace (1982:113) ገልፀዋል፡፡ ለቃላት ትምህርት አቀራረብ አውድ ትልቅ ድርሻ እንዳለው እና ለቋንቋ ተማሪዎች ተገቢ የሚሆነው የማስተማሪያ ዘዴም ተማሪዎች ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ የሚጋለጡበትን አውድ ማመቻቸትና የአዳዲስ ቃላትን ፍች ከአውዳቸው መገመት እንዲችሉ መገፋፋት መሆኑን ነው፡፡

***ሠንጠረዥ 3፡ ቃላትን በአውድ ከማስተማር አንፃር በተደረገ ምልከታ የተገኘ መረጃ***

| ተ.ቁ | የምልከታ መስፈርቶች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ለተማሪዎች የቃላትን ትምህርት በአውዳዊ አገባብ መሰረት አድርጎ ከማስተማር አንፃር | | | 1 | 2 | |

ቃላትን በአውድ ከማስተማር አንፃር በምልከታ የተገኘው መረጃ 2 (66.66)መምህራን በከፍተኛ 1 መምህር (33.33)በመካከለኛ በሆነ ደረጃ ሲጠቀሙበት ተስተውለዋል፡፡

*ሠንጠረዥ 4፡ ቃላትን በአውድ ከማስተማር አንፃር ለመምህራን ለቀረበ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ*

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ቃላትን በአውድ አስተምራለሁ | | | | | 3 |

የቃላት ትምህርትን አውድን መሰረት አድርጎ ማስተማር በተመለከተ ለመምህራን በቀረበ ጥያቄ ቃላትን በአውድ መሰረት አድርጌ አስተምራለሁ ለሚለው የመምህራን ምላሽ 3 መምህራን (100%) በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያስተምሩ መልሰዋል፡፡

*ሠንጠረዥ 5፡ ቃላትን በአውድ ከማስተማር አንፃር ለተማሪዎች በቀረበ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ*

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % |
| 3 | የቃላትን ትምህርት በአውዳዊ አገባብ ያስተምሯችኃል | 7 | 6.66 | 13 | 12.38 | 21 | 20 | 55 | 52.38 | 9 | 8.57 |

ተማሪዎች አንድን ቃል ያለችግር እንዲገለገሉበትና ስለፍቺው በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከተፈለገ በተቻለ አቅም ቃሉን በተደጋጋሚ እና በተለያየ አውድ ውስጥ ሊያገኙት ይገባል Cunningsworth (1995) ፡፡ በዚህ ጥናት አጥኚው ለተማሪዎች የቃላትን ትምህርት በአውዳዊ አገባብ ያስተምሯችኃል? ተብሎ ለቀረበላቸው የፅሑፍ መጠይቅ 9ተማሪዎች (8.57%)በጣም ከፍተኛ፤ 55ተማሪዎች (52.38%) ከፍተኛ፤ 21ተማሪዎች (20%) መካከለኛ ፤13ተማሪዎች (12.38%) ዝቅተኛ እና 7ተማሪዎች (6.66%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ የቃላትን ትምህርት እንደሚማሩ መልሰዋል፡፡

### 4.3.2 ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት ማቅረብ

ተማሪዎች በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ ላይ እያሉ ቃላትን በዝምድናቸው መነሻነት ማቅረብ በቀላሉ የቃልን ፍች እንዲገነዘቡ ያደጋል በማለት McCarthy (1990፣39) ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪ Bahuer (1998፣31-34) ቃላትን በተመሳስሏቸውና በተቃርኗቸው፣ በቃላት አካታችና ተከታች ግንኙነት እንዲሁም በአብሮ ተሰላፉነታቸው ለይቶ ማቅረብ ተገቢ ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

**ሠንጠረዥ 6፡ ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት ከማቅረብ አንፃር በተደረገ ምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ | የምልከታ መስፈርቶች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት አድረገው ከማስተማር አንፃር | | | | | |
| 1.1 | የቃላትን ተመሣሣይ እና ተቃራኒ ፍችቻቸው ስለመማራቸው | | | | 1 | 2 |
| 1.2 | ቃላትን አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ቃላትን ትምህርት መምህሩ ስለመቅረቡ | 2 | 1 | | | |
| 1.3 | አብሮ ተሰላፊ ቃላትን መሰረት አድርጎ የቃላትን ትምህርት ስለመማራቸሁ | | 2 | 1 | | |

ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት አድረጎ ከማስተማር ውስጥ አንዱ የቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍቻቸው ማስተማር ሲሆን ክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ 2 (66.66%) መምህራን በጣም ከፍተኛ 1 መምህር (33.33%) በከፍተኛ ደረጃ ሲያስተምሩ ተስተውሏ፡፡ ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካይነት አድረጎ ከማስተማር ውስጥ ሌላኛው የቃላትን አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ቃላትን ትምህርት ማስተማር ሲሆን በዚህም 1 መምህር (33.33%) በዝቅተኛ 2 መምህራን (66.66%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ሲያስተምሩ ተስተውሏ፡፡ በተጨማሪ ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካይነት አድረጎ ከማስተማር አንፃር አብሮ ተሰላፊ ቃላትን መሰረት አድርጎ የቃላትን ትምህርት ማስተማር

ሲሆን ይህም 1 መምህር (33.33%) በመካከለኛ 2 መምህራን (66.66%) በዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ሲያስተምሩ ተስተውሏል፡፡

### ሠንጠረዥ 7፡ *ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት ከማቅረብ አንፃር ለመምህራን በቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ*

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1 | ቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍቻቸው አቀርባለሁ | | | | | 3 |
| 2.2 | የቃላትን አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጌ ቃላትን ትምህርት አቀርባለሁ | | | 2 | 1 | |
| 2.3 | አብሮ ተሰላፊ ቃላትን መሰረት አድርጎ ቃላትን አስተምራለሁ | | | | 2 | 1 |

ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት አድረጎ ከማስተማር ውስጥ አንዱ የቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍችቻቸው ማስተማር ሲሆን ለመምህራን በቀረበ ጥያቄ 3ቱም መምህራን (100%) በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል፡፡ የቃላትን አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ቃላትን ትምህርት ማስተማር በተመለከተ 1 መምህር (33.33%) በከፍተኛ 2 መምህራን (66.66%) በመካከለኛ በሆነ ደረጃ እንደሚያስተምሩ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪ ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካይነት አድረጎ ከማስተማር አንፃር ስር አብሮ ተሰላፊ ቃላትን መሰረት አድርጎ የቃላትን ትምህርት ማስተማር በተመለከተ 1 መምህር (33.33%) በጣም በከፍተኛ 2 መምህራን (66.66%) በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያስተምሩ መልሰዋል፡፡

***ሠንጠረዥ 8፡ ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት ከማቅረብ አንፃር ለተማሪዎች ለቀረበ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ***

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 3 | ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት ከማቅረብ አንፃር | | | | | | | | | | |
| 3.1 | የቃላትን ተመሣሣይ እና ተቃራኒ ፍችቻቸው ትማራላችሁ | 3 | 2.85 | 2 | 1.9 | 15 | 14.28 | 26 | 24.76 | 59 | 56.19 |
| 3.2 | ቃላትን አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ቃላትን ትምህርት መምህሩ ያስተምሯችኃል | 63 | 60 | 25 | 23.8 | 12 | 11.42 | 2 | 1.9 | 3 | 2.85 |
| 3.3 | አብሮ ተሰላፊ ቃላትን መሰረት አድርጎ የቃላትን ትምህርት ትማራላቹ | 38 | 36.2 | 27 | 25.71 | 26 | 24.76 | 6 | 5.71 | 8 | 7.67 |

ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት ከማስተማር ስልቶች መካከል ከሚጠቀሱት አንዱ ቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍችቻቸው ማስተማር ሲሆን ተማሪዎች ቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍቻቸው ትማራላችሁ? ተብሎ በቀረበ ጥያቄ 59 ተማሪዎች (56.19%) በጣም ከፍተኛ፣26 ተማሪዎች (24.76%) ከፍተኛ፣15 ተማሪዎች (14.28%) መካከለኛ፣2 ተማሪዎች (1.90%) ዝቅተኛ እና 3 ተማሪዎች (2.85%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚማሩ መልሰዋል፡፡ ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት አድረጎ ማስተማር ሌላው የቃላትን አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ የቃላትን ትምህርት ማስተማር

ሲሆን የቃላት አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ቃላትን ትምህርት መምህሩ ያስተምሯችኋል? በሚል ለቀረበ ጥያቄ 3 ተማሪዎች (2.85%) በጣም ከፍተኛ፣2 ተማሪዎች (1.90%) ከፍተኛ፣12 ተማሪዎች (11.42%) መካከለኛ፣25 ተማሪዎች (23.80%) ዝቅተኛ እና 63 ተማሪዎች (60%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚማሩ መልሰዋል። ቃላትን በፍች ተዛምዷቸው አማካይነት አድረጎ ማስተማር ውስጥ ሌላው አብሮ ተሰላፊ ቃላትን መሰረት አድርጎ ቃላትን ማስተማር ሲሆን አብሮ ተሰላፊ ቃላትን መሰረት ተደርጎ የቃላትን ትምህርት ትማራላቹ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ 8 ተማሪዎች (7.87%) በጣም ከፍተኛ፣6 ተማሪዎች (5.71%) ከፍተኛ፣26 ተማሪዎች (24.76%) መካከለኛ፣27 ተማሪዎች (25.71%) ዝቅተኛ እና 38 ተማሪዎች (36.19%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚማሩ መልሰዋል።

### 4.3.3 የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ቃላትን ማቅረብ

**ሠንጠረዥ 9፡ *የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ቃላትን ከማቅረብ አንፃር በተደረገ ምልከታ የተገኘ መረጃ***

| ተ.ቁ | የምልከታ መስፈርቶች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቃላትን ትምህርት በእርባታ እና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርገሀ ከማስተማር አንፃር | | 1 | 1 | 1 | |

የቃላትን ትምህርት በእርባታ እና በምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ከማስተማር አንፃር በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ 1 መምህር (33.33%) በከፍተኛ፣1መምህር.(33.33%) በመካከለኛ እና 1መምህር (33.33%) በዝቅተኛ ደረጃ ሲያስተምሩ ተስተውሏ።

**ሠንጠረዥ 10፡ *የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ቃላትን ከማቅረብ አንፃር ለመምህራን በቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ***

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ቃላትን የእርባታ እና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጌ አቀርባለሁ | | | | 2 | 1 |

ቃላትን በእርባታ እና በምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ከማቅረብ አንፃር ለመምህራን ለቀረበ ጥያቄ 1መምህር (33.33%) በጣም በከፍተኛ እና 2መምህራን (66.66%) በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያስተምሩ መልሰዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 11፡ *የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ቃላትን ከማቅረብ አንፃር ለተማሪዎች በቀረበ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ***

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁ ጥር | % | በቁጥ ር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % |
| 3 | የቃላትን ትምህርት በእርባታና በምስረታ ስርዓትመሰረት አድርገው ያስተምሯችኋል | 19 | 18. 09 | 8 | 7.6 1 | 38 | 36.1 9 | 27 | 25. 71 | 13 | 12. 38 |

በቃላት የእርባታና ምስረታ ሂደት ላይ ያተኮረ ትምህርት ተማሪዎች ቃላትን ለመረዳትም ሆነ ለማፍለቅ እንዲችሉ መሠረት እንደሚጥልላቸው ይጠቁማሉ፡፡ እንዲሁም የቃላት ትምህርት ከመረዳት አንፃር ሲታይ፣ ተማሪዎች የማያውቁት ቃል ሲገጥማቸው የቃሉን ስነ-ምዕላዳዊ አወቃቀር እና የቃሉን ፍች መመርመር እንዲችሉ ፍንጭ ይሰጣሉ Gaims እና Redman (1986፣48)፡፡ ቃላትን በእርባታና በምስረታ ስርዓት መሰረት አድርገው ያስተምሯችኃል? ተብሎ ለቀረበ ጥያቄ 13 ተማሪዎች (13.38%) በጣም ከፍተኛ፣27 ተማሪዎች (25.75%) ከፍተኛ፣38 ተማሪዎች (36.19%) መካከለኛ፣8 ተማሪዎች (7፣61%) ዝቅተኛ እና 19 ተማሪዎች (18.09%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ የቃላትን ትምህርት በእርባታ እና በምስረታ ስርዓት መሰረት ተደርጎ እንደሚማሩ መልሰዋል፡፡

### 4.3.4 የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ

***ሠንጠረዥ 12፡ የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ አንፃር በተደረገ ምልከታ የተገኘ መረጃ***

| ተ.ቁ | የምልከታ መስፈርቶች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፈው ከማስተማር አንፃር | | | 2 | 1 | |

የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ አንፃር በተደረገ ምልከታ 1 መምህር.(33.33%) በከፍተኛ እና 2 መምህራን (66.66%) በመካከለኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙት ተስተውሏል፡፡

***ሠንጠረዥ 13፡ የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ አንፃር ለመምህራን በቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ***

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፌ አቀርባለሁ | | | | | 3 |

የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ አንፃር ለመምህረን በቀረበ ጥያቄ 3 መምህራን (100%) በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚጠቀሙ መልሰዋል፡፡

***ሠንጠረዥ 14፡ የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ አንፃር ለተማሪዎች በቀረበ ጥያቄ የተገኘ ምላሽ***

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 3 | የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ያቀርቡሏችኋል | 11 | 10.47 | 4 | 3.80 | 8 | 7.61 | 43 | 40.95 | 39 | 37.14 |

የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ያቀርቡላችኋል? ተብሎ ለቀረበ ጥያቄ 39 ተማሪዎች (37.14%) በጣም ከፍተኛ፣ 43 ተማሪዎች (40.95%) ከፍተኛ፣8 ተማሪዎች (7.61%) መካከለኛ፣4 ተማሪዎች (3.80%) ዝቅተኛ እና 11 ተማሪዎች (10.47%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት ተደግፎ እንደሚማሩ መልሰዋል፡፡

### 4.3.5 ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ

ሠንጠረዥ 15፡ *ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ በተመለከተ በተደረገ ምልከታ የተገኘ መረጃ*

| ተ.ቁ | የምልከታ መስፈርቶች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቃላትን ቋንቋ ከክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ከማስተማር አንፃር | | | | 1 | 2 |

ቃላትን ከክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ከማስተማር አንፃር በተደረገ የክፍል ውስጥ ምልከታ 2 መምህራን (100%).በጣም ከፍተኛ እና 1 መምህር(33.33%) ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ሲያስተምሩ ተስተውሏ፡፡

ሠንጠረዥ 16፡ *ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ በተመለከተ ለመምህራን በቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ*

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ቃላትን ከክሂሎች ጋር አቀናጅቼ አስተመራለሁ | | | | | 3 |

ቃላትን ከክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ከማስተማር አንፃር ለመምህራን ፡-ቃላትን ከክሂሎች ጋር አቀናጅቼ አስተምራለሁ በሚል ለቀረበ ጥያቄ 3ቱም መምህራን(100%) በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚጠቀሙ መልሰዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 17፡ *ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ በተመለከተ ለተማሪዎች በቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ***

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 3 | ቃላትን ከክሂሎች ጋር አቀናጅተው ያስተምሯችኋል | 2 | 1.9 | 5 | 4.76 | 44 | 41.9 | 22 | 20.95 | 32 | 30.47 |

ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ በተመለከተ ለተማሪዎች በቀረበ ጥያቄ 2 ተማሪዎች (1.90%) በጣም ከፍተኛ፣22 ተማሪዎች (20.95%) ከፍተኛ፣5 ተማሪዎች (4.76%) መካከለኛ፣44 ተማሪዎች (41.90%) ዝቅተኛ እና 32 ተማሪዎች (30.47%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ የቃላትን ትምህርት ከክሂሎች ጋር በማጣመር ቃለትን እንደሚማሩ መልሰዋል፡፡

### 4.3.6 ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ማቅረብ

**ሠንጠረዥ 18፡ *ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር በተመለከተ በተደረገ ምልከታ የተገኝ መረጃ***

| ተ.ቁ | የምልከታ መስፈርቶች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መምህራን ምንባብ በማዘጋጀት ቃላትን ከማስተማር አንፃር | 2 | 1 | | | |

መምህራን ምንባብ በማዘጋጀት ቃላትን ከማስተማር አንፃር በተደረገ ክፍል ውስጥ ምልከታ ምልከታ 1 መምህር (33.33%) በዝቅተኛ እና 2 መምህራን (66.66%)በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚጠቀሙት ተስተውሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 19፡ *ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር በተመለከተ ለመምህራን በቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ***

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ምንባብ በማዘጋጀት ቃላትን አስተምራለሁ | | | 1 | 2 | |

ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር በተመለከተ ለመምህራን በቀረበ ጥያቄ 2መምህራን (66.66%) ከፍተኛ እና 1መምህር (33.33%) በመካከኛ በሆነ ደረጃ እንደሚጠቀሙ መልሰዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 20፡ *ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር በተመለከተ ለተማሪዎች በቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ***

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 3 | መምህራን ምንባብ በማዘጋጀት ቃላትን ያስተምሯችኋል | 27 | 25.75 | 35 | 33.33 | 25 | 23.8 | 10 | 9.52 | 8 | 7.61 |

መምህራን ምንባብ በማዘጋጀት ቃላትን ያስተምሯችኋል? ተብሎ ለቀረበ ጥያቄ 8 ተማሪዎች (7.62%) በጣም ከፍተኛ፣10 ተማሪዎች (9.52%) ከፍተኛ፣25 ተማሪዎች (23.80%) መካከለኛ፣35 ተማሪዎች (33.33%) ዝቅተኛ እና 27 ተማሪዎች 25.75%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ መምህራን ምንባብ በማዘጋጀት ቃላትን ትምህርት እንደሚያስተሙሯቸው መልሰዋል፡፡

### 4.3.7 ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላትን ማስተማር

*ሠንጠረዥ 21፡ ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላትን ማስተማር በተመለከተ በተደረገ ምልከታ የተገኘ መረጃ*

| ተ.ቁ | የምልከታ መስፈርቶች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላት ከማስተማር አንፃር | | | 2 | 1 | |

ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላትን ማስተማር በተመለከተ የተደረገ የክፍል ውስጥ ምልከታ 1 መምህር (33.33%) ከፍተኛ እና 2 መምህራን (66.66%) መካከለኛ በሆነ ደረጃ ሲያስተምሩ ተስተውሏ፡፡

*ሠንጠረዥ 22፡ ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላትን ማስተማር በተመለከተ ለመምህራን በቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ*

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላት አስተምራለሁ | | | | | 3 |

ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላትን ማስተማር በተመለከተ ለመምህራን በቀረበ ጥያቄ 3ቱም መምህራን (100%) በጣም ከፍተኛ ብለው መልሰዋል፡፡

*ሠንጠረዥ 23፡ ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላትን ማስተማር በተመለከተ ለተማሪዎች ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ*

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 3 | ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላት ትማራላች | 5 | 4.76 | 6 | 5.71 | 37 | 35.23 | 30 | 28.57 | 27 | 25.7 |

ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላት ትማራላችሁ? ተብሎ ለቀረበ ጥያቄ 27 ተማሪዎች (25.71%) በጣም ከፍተኛ፣30 ተማሪዎች (28.57%) ከፍተኛ፣37 ተማሪዎች (35.23%) መካከለኛ፣6 ተማሪዎች (5.71%) ዝቅተኛ እና 5 ተማሪዎች (4.76%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ መምህራን ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላት እንደሚማሩ መልሰዋል፡፡

### 4.3.8 ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ

**ሠንጠረዥ 24፡ *ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ በተመለከተ በተደረገ ምልከታ የተገኘ መረጃ***

| ተ.ቁ | የምልከታ መስፈርቶች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቃላትን ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ስለመቅረቡ | 1 | 2 | | | |

ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ በተመለከተ የተደረገ የክፍል ውስጥ ምልከታ 2መምህራን (66.66%) በዝቅተኛ እና 1 መምህር (33.33% )በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ሲያስተምሩ ተስተውሏ፡፡

**ሠንጠረዥ 25፡ *ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት በተመለከተ ለመምህራን በቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ***

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ቃላትን ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት አቀርባለሁ | | | 3 | | |

ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት በተመለከተ ለመምህራን በቀረበ ጥያቄ 3ቱም መምህራን (100%)በመካከለኛ ደረጃ እንደሚጠቀሙ መልሰዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 26፡ *ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ በተመለከተ ለተማሪዎች በቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ***

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁጥ ር | % | በቁ ጥር | % |
| 3 | ቃላትን ሀረጎችን ለመረዳትናለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ያቀርቡሏችኋል | 34 | 32.38 | 45 | 42.85 | 18 | 17.14 | 7 | 6.66 | 1 | 0.95 |

ቃላትን ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ያቀርቡሏችኋል? ተብሎ ለቀረበ ጥያቄ 1ተማሪ (0.95%) በጣም ከፍተኛ፣7 ተማሪዎች (6.66%) ከፍተኛ፣18 ተማሪዎች (17.14%) መካከለኛ፣45 ተማሪዎች (42.85%) ዝቅተኛ እና 34 ተማሪዎች (32.38%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ መምህራን ቃላትን ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ያቀርቡሉናል በማለት መልሰዋል፡፡

### 4.4 በቃላት ትምህርት የተማሪዎች ተሳትፎ በተመለከተ

**ሠንጠረዥ 27፡ *በቃላት ትምህርት መምህሩ ተማሪዎችን ማሳተፉ በተመለከተ በተደረገ የክፍል ኃላፊ ውስጥ ምልከታ የተገኘ መረጃ***

| ተ.ቁ | የምልከታ መስፈርቶች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መምህሩ ተማሪዎች የማሳተፍ ተግባሩ | | 2 | 1 | | |

መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቃላትን ሲያስተምሩ ተማሪዎች የማሳተፍ ተግባራቸው ምን ያህል ነው?ለሚለው በተደረገ የክፍል ውስጥ ምልከታ 1መምህር (33.33) መካከለኛ እና 2 መምህራን (66.66%) ዝቅተኛ በሆነ መልኩ ተማሪዎችን እንደሚያሳትፉ ተመልክቷል፡፡

*ሠንጠረዥ 28፡ በቃላት ትምህርት የተማሪዎች ተሳትፎ በተመለከተ ለተማሪዎች ለቀረበ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ*

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 2 | የቃላት ትምህርትን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ስትማሩ ትሳተፋላችሁ | 3 | 2.85 | 1 | 0.95 | 12 | 11.42 | 32 | 30.47 | 57 | 54.28 |

የቃላት ትምህርትን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ስትማሩ ትሳተፋላችሁ ተብሎ ለቀረበ ጥያቄ የቀረበ ጥያቄ 57 ተማሪዎች (54.28%) በጣም ከፍተኛ፣32ተማሪዎች (30.47%) ከፍተኛ፣ 12ተማሪዎች (11.42%) መካከለኛ፣1ተማሪ (0.95%) ዝቅተኛ እና 3 ተማሪዎች(2.85%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚሳተፉ መልሰዋል፡፡

## 4.5 በቃላት ትምህርት አተገባበር ላይ የሚያጋጥሙ ተለዋዋጮች

በምዕራፍ ሁለት በቃላት ትምህርት አተገባበር ላይ የሚያጋጥሙ ተፅዕኖዎች በተመለከተ ደረበ (1994) የWest (1963) ጥናት በመጥቀስ ችግሮቹን ከመምህራን፣ከተማሪና ከማስተማሪያ ግብኣቶች አንፃር በማለት ተጠቅሰዋል፡፡

በዚህ ጥናት መምህራን በተመለከተ በቃላት ትምህርት አቀራረብ ና አተገባበር ላይ የሚያጋጥሙ ተለዋዋጮች በቃለ መጠይቅና በምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚገልጹት፡- መዝገበቃላት የመጠቀም ልምድ ያለመኖር፣ ቃላት የማስተማሪያ መንገዶች በአብዛኛው ያለመጠቀም፣ መምህራን ሲያስተምሩ የድምፅ አለመሰማት፣ መፍጠን፣መምህራን ቃላትን ሲፅፉ የፊደል ግድፈት መኖር፣ የቃላት ትምህርት ቀላል አድርጎ የማየት፣ በቂ የሆነ ስልጠና ያለማግኘት፣የማስተማር ስነዘዴ ኮርስ(PGDT) ያለመውሰድ የሚሉትን ችግሮች እንደሆኑ ተገልጸዋል፡፡

ተማሪዎችን በተመለከተ በቃላት ትምህርት አቀራረብ እና አተገባበር ላይ የሚያጋጥሙ ተለዋዋጮች በጽሑፍ መጠይቅና በምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚገልፁት፡-አንዳንድ ተማሪዎች የቃላትን ፍችቻቸውን ያለማወቅ፣ መዝገበቃላት የመጠቀም ልምድ ያለመኖር፣ቃላትን በተመለከተ የሚሰጥ የቤት ስራዎችን ያለመስራት፣ ሲጠየቁ ያለመመለስ፣ የተማሪዎች ቁጥር ብዛት ለክትትል ምቹ ያለመሆን ፣ትኩረት ማጣት፣ፍራቻና ሚናገሩትን ማጣት ፣ተማሪዎች ቃላትን አቀላጥፎ ያለመናገር፣መረበሽ፣ አለመረዳትና ግራ መጋባት፣ ቃላቶችን በአግባቡ ያለመጥራት፣የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅኖ የሚሉትን ችግሮች እንደሆኑ በቃለ መጠይቅና በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ይገልጻል፡፡

ከማስተማሪያ ግብኣቶች በተመለከተ በጽሑፍ መጠይቅና በምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚገልፁት፡-የመምህራን መሪ መፅሐፍ እና የተማሪዎች መማሪያ መፅሐፍ በበቂ ሁኔታ ያለማሟላት የሚሉ በቃለ መጠይቅና በምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በጽሑፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ እንደሚገልፀው መምህራን በቃላት ማስተማር ሂደት የሚያጋጥማቸውን ችግር ለተማሪዎች ምክር በመስጠት፣ በማበረታታት፣ የቤት ስራዎችን በማረም እና የቤት ስራዎችን ውጤት በመስጠት፣ቤተ መፅሐፍት መፅሐፎችን በማስቀመጥ እንዲጠቀሙ በማድረግ፣ቀለል ባለ መልኩ በማስተማር ችግሩን ለመቅረፍ እንደሚሞክሩ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪ ተማሪዎች የቃላት ትምህርት የራሱ የሆነ ምዕራፍ ቢኖረው ፣መምህራኖች ትኩረት አድርገው እንዲያስተምሩ እና ከመማሪያ መፅሐፉ በተጨማሪ አጋዥ በሆኑ ሰነዶችን አዘጋጅተው ቢያስተምሩ የሚሉ አስተያየቶችን ጠቅሰዋል፡፡

### 4.6 የጥናቱ የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ትኩረት በጉራጌ ዞን በቡታጀራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል መምህራን ተተኳሪ ያደረገ የቃላት ትምህርት አተገባበር ትንተና ሲሆን በዚህ አብይ አላማ ስር ጥናቱ ያነሳቸው መምህራን የትኛውን የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶችን ይበልጥ ይጠቀማሉ እና የክፍል ውስጥ የአተገባበር ሂደት ምን ይመስላል እንዲህም ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ያላቸው ተሳትፎ ምን ያህል ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ከመምህራንና ከተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቆች እና በምልከታ መረጃዎች

ተሰብስቧል፡፡ የተሰበሰበው መረጃም በሰንጠረዥ በመቶኛና በቃላት አማካኝነት በገላጭ የትንተና ስልት ተተንትነዋል፡፡ ጥናቱ ያስገኛቸው ውጤቶችም ቀርበዋል፡፡

የመማር ሥልቶች ላይ እንደሚያሳዩት በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የቃላት ማቅረቢያ ዘዴዎችን አስተዋውቀዋል፡፡ ከእነዚህ የቃላት ማቅረቢያ ስልቶች መካከልም ዋና ዋና የሚባሉት ቃላትን በአውድ ማቅረብ፤ ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው ማቅረብ (ቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍቺ ማቅረብ፣የቃላትን አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ እና የቃላት አብሮ ተሰላፊነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ)፤ የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ማቅረብ፤ የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ፤ ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ ፣ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳት ና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ፤ቃላትን ግልፅ በሆነ መመሪያዎችን ማቅረብ እና ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ማቅረብ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በመሆኑም በዚህ ጥናት የቃላት ማቅረቢያ መንገዶች በተመለከተ በምልከታ የተገኘው ውጤት ተተንትኖ እንዳሳየው፡-በአውድ ማቅረብ፤ ቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍቺ ማቅረብ፣ የቃላት ቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ፤ ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ በመመዘኛነት በተቀመጠው መስፈርት ከፍተኛ እንደሚገኝ አሳይተዋል፡፡ የቃላትን አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ እና የቃላት አብሮ ተሰላፊነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ እና ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ማቅረብ ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ተገኝቷል፡፡

የቃላት ማቅረቢያ መንገዶች በተመለከተ ለመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት ተተንትኖ እንዳሳየው፡-በአውድ ማቅረብ፤ ቃላትን በፍቺ ዝምድናቸው ማቅረብ(ቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍቺ ማቅረብ፣የቃላትን አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ እና የቃላት አብሮ ተሰላፊነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ)፤ የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ማቅረብ፤ የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ፤ ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ ፣ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳት ና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ ፤ቃላትን ግልፅ በሆነ መመሪያዎችን ማቅረብ እና ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ማቅረብ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚገኝ አሳይተዋል፡፡

በዚህ ጥናት የቃላት ማቅረቢያ መንገዶች በተመለከተ ለተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት ተተንትኖ እንዳሳየው፡-በአውድ ማቅረብ፤ ቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍቺ ማቅረብ እና የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ በመመዘኛነት በተቀመጠው መስፈርት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚገኝ አሳይተዋል፡፡ የቃላትን አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ እና የቃላት አብሮ ተሰላፊነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ፤ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳት ና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ ፤ቃላትን ግልፅ በሆነ መመሪያዎችን ማቅረብ እና ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ማቅረብ ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ተገኝቷል፡፡

ሌላው የዚህ ጥናት አላማ የቃላት ትምህርት አተገባበር በተመለከተ የተገኘው ውጤት ተተንትኖ እንዳሳየው፡- መምህራን አላማን መሰረት ያደረጉ እና ቃላትን በተመሳሳይ ባህሪያቸው፣ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ፣በሚኖራቸው የፍቺ ተዛማዶ እና በፍች ተቃርኖ ማቧግኖ ማቅረብ በተመለከተ ከማስተማር አንፃር ከፍተኛ ሆነው ታይቷል፡፡ የቃላት ትምህርት ይዘት ከክፍለ ጊዜ እና ከተማሪዎች ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ እና የቃላትን ትምህርት ለትውስታ በሚመች መልኩ ማስተማር መካከለኛ እንዲሁም ቃላትን ለትንበያ በሚመች መልኩ ከማቅረብ አንፃር እና ሁኔታዊ አቀራረብ ተከትሎ ከማስተማር አንፃር ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሌላው የዚህ ጥናት አላማ ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ያላቸው ተሳትፎ በተመለከተ ተተንትኖ በተገለፀው መረጃ ተማሪዎች ከፍተኛ በሆነ መልኩ እንደሚሳተፉ እና መምህራንም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚያሳትፉ ቢገልፁም በምልከታ በተገኘው መረጃ እንደተተነተነው መምህራን ሲያስተምሩናተማሪዎች ሲማሩ ዝቅተኛ የሆነ ተሳትፎ መኖሩን በምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ይህ ጥናት ከሌሎች ጥናቶች ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት መመልከት ይቻላል፡፡ ደረበ ሙሉ (1999) በትግረኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቃላት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ በሚል ርዕስ የተደረገ ጥናት ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር የቃላት ትምህርት አቀራረብ ላይ ማጥናቱ፤የዘጠነኛ የክፍል ደረጃ እና የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ማተኮሩ ያመሳስላቸዋል፡፡ የደረበ ጥናት መምህራን ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጉ፤ በሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናቱ ማካሄዱ እና አፋቸውን በትግርኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች ላይ ማተኮሩ ይህ ጥናት ደግሞ ከመምህራን በተጨማሪ ተማሪዎች ላይም ትኩረት ማድረጉ እና በአንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ

ጥናት ያደረገ መሆኑ፣ የቃላት ትምህርት አቀራረብ በተጨማሪ የቃላት ትምህርት አተገባበር ላይ ማጥናቱ ከዚህ ጥናት ያለያያቸዋል፡፡

አድኗል ደባልቄ (2013) አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ ሰባተኛ ክፍል የቃላት ትምህርት አተገባበር ፍተሻ በሚል የቀረበ ጥናት ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር የቃላት ትምህርት አተገባበር እና መምህራን ላይ ትኩረት መስጠቱ ያመሳስላቸዋል፡፡ ይህ ጥናት በቃላት ትምህርት የተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ማጥናቱ እና ዘጠነኛ ክፍል ማተኮሩ ላይ ከአድኗል ጥናት ያለያያቸዋል፡፡

የብሩክታዊት ተስፋዬ(2001) በመቀሌ ከተማ በሚገኙ በሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የቃላት ትምህርት አተገባበር ፍተሻ በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር የቃላት ትምህርት አተገባበር ላይ ማጥናቱ፤የዘጠነኛ የክፍል ደረጃ እና የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ማተኮሩ ያመሳስላቸዋል፡፡ የብሩክታዊት ጥናት የቃላት ትምህርት አተገባበር ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጉ፤ በሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናቱ ማካሄዱ ይህ ጥናት ደግሞ ከመምህራን በተጨማሪ ተማሪዎች ላይም ትኩረት ማድረጉ እና በአንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ጥናት ያደረገ መሆኑ፣ የቃላት ትምህርት አተገባበር በተጨማሪ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ላይ ማጥናቱ ከዚህ ጥናት ያለያያቸዋል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ እና አስተያየት

### 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ዋና አላማው በቡታጀራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ የክፍል የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ትምህርት አተገባበር ትንተና ሲሆን በዚህ አብይ አላማ ስር መምህራን የትኛውን የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶችን ይበልጥ ይጠቀማሉ እና የክፍል ውስጥ የአተገባበር ሂደት ምን ይመስላል እንዲሁም ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ያላቸው ተሳትፎ ምን ያህል ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ለመመለስ መሰረት አድረጎ ተነስቷል፡፡ ጥናቱ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ ለመረጃ ምንጭነትም በጉራጌ ዞን ካሉ ትምህርት ቤቶች መካከል በቡታጀራ ከተማ በህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመርጠዋል፡፡ በትምህርት ቤቱ ካሉ ከዘጠኝ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች እና የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጥናቱ በማካተት የክፍል ውስጥ ምልከታ እና የጽሑፍ መጠይቆች ከመምህራን እና ከተማሪዎች መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ መረጃዎችን ለመተንተንም በገለፃ ላይ የተመሠረተ አቀራረብ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ከዚያም የተገኘውን ውጤት እንደሚከተለው ለማጠቃለል ተሞክሯል፡፡

የቃላት ትምህርት ማስተማሪያ መርሖች በተመለከተ መምህራን ስለሚያስተምሩት የቃላት ትምህርት አላማ ግንዛቤው እንዳላቸው እና ቃላትን በተመሳሳይ ባህሪያቸው፣ በሚያነሱት ርዕስ ጉዳይ፣በሚኖራቸው የፍች ተዛማዶ እንዲሁም በፍች ተቃርኖ አቧድኖ ከማቅረብ አንፃር ከፍተኛ በሆነ ደረጃ መሆኑን አጥኚው ተገንዝቧል፡፡ ሁኔታዊ አቀራረብ ተከትሎ ከማስተማር አንፃር ፣ ይዘቶቹ ከክፍለ ጊዜው እንዲሁም ከተማሪዎች ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ፣የቃላትን ትምህርት ለትውስታ በሚመች መልኩ ከማስተማር አንፃር ፣መምህራን ተማሪዎቻቸው የቃላት ችሎታቸውን በራሳቸው ጥረት እንዲያሳድጉና እንዲማሩ በዐውድ ውስጥ ቃላት እንዴት ፍችቻቸውን መተንበይ እንዳለባቸው እና ቃላትን ለትንበያ በሚመች መልኩ ከማስተማር አንፃር መካከለኛ በሆነ ደረጃ እንደሚገኝ አጥኚው ተገንዝቧል፡፡

የቃላት ማስተማሪያ መንገዶች መካከል ቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍች ማቅረብ ፣ቃላትን በአውድ ማቅረብ እና ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ከማቅረብ አንፃር ከፍተኛ በሆነ መልኩ እንደሚጠቀሙ አጥኚው ተገንዝቧል፡፡ ቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት

መሰረት አድርጎ ማቅረብ፣ የቃላት ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ እና ቃላትን ግልፅ በሆነ መመሪያ ከማቅረብ አንፃር መካከለኛ በሆነ መልኩ እንደሚጠቀሙ አጥኚው ተገንዝቧል፡፡ እንዲሁም የቃላት አብሮ ተሰላፊነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ ፣ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳት እና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ ፣የቃላት አካታች ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ እና ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚጠቀሙባቸው አጥኚው ተገንዝቧል፡፡

በቃላት ትምህርት መምህራን እንደሚያሳተፉ እና ተማሪዎች እንደሚሳተፉ ቢመልሱም አጥኚው በምልከታ እንዳረጋገጠው ተማሪዎች ዝቅተኛ ተሳትፎ እንዳላቸው እና መምህሩ ተማሪዎችን የማሳተፍ ተግባሩ ዝቅተኛ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

መምህራን እለታዊ እቅድ መሰረት በማድረግ እንደሚዘጋጁ፤ ቃላትን ለማስተማር የመማሪያ መጽሐፍ መሰረት በማድረግ እንደሚያቀርቡ፤ የቃላትን ፍች አውድ መሰረት በማድረግ፣ የቃላትን ፍች ለተማሪዎች የቤት ስራ በመስጠት ፣ የተለያዩ ቀላል ምሳሌዎች በመስጠት እንደሚተገብሩ እና ቃላትን የማስተማሪያ መንገዶች እንደ ክፍለ ጊዜው እና እንደ እለቱ ትምህርት መርጠው እንደሚጠቀሙ ከጥናቱ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በአንፃሩ መምህራን የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመምህሩ መማሪያ መፅሐፍ በእጃቸው እንደሌለ፤ አጋዥ የሆኑ የማስተማሪያ ሰነዶችን እንደማያዘጋጁ፤የቃላት ትምህርት በተመለከተ ስልጠናዎችን ወስደው እንደማያውቁ ፣የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ፣ለቋንቋው የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ማነስ ፣የመጽሐፍ እጥረት፣የመምህሩ መሪ መጽሐፍ ያለመኖር እና ተማሪዎች ሲጠየቁ ያለመመለስ፣ የቤት ስራ ያለመስራት፣ፍራቻ ለቃላት ትምህርት ተግዳሮቶች መሆናቸው አጥኚው ከጥናቱ ውጤት ለመገንዘብ ችሏል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

መምህራን ስለሚያስተምሩት የቃላት ትምህርት አላማው በተመለከተ፤ ቃላትን በተመሳሳይ ባህሪያቸው፣ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ፣በሚኖራቸው የፍች ተዛማዶ እንዲሁም በፍች ተቃርኖ አቧድኖ ከማቅረብ አንፃር የተሻለ ግንዛቤ እንዳላቸው በአንፃሩ ሁኔታዊ አቀራረብ ተከትሎ ከማስተማር አንፃር ፤ ይዘቶቹ ከክፍለ ጊዜው እንዲሁም ከተማሪዎች ጋር አጣጥሞ ከማስተማር አንፃር ፤የቃላትን ትምህርት ለትውስታ በሚመች መልኩ ከማስተማር አንፃር ፤መምህራን ተማሪዎቻቸው የቃላት ችሎታቸውን በራሳቸው ጥረት እንዲያሳድጉና እንዲማሩ

በዐውድ ውስጥ ቃላት እንዴት ፍችቻቸውን መተንበይ እንዳለባቸው እና ቃላትን ለትንበያ በሚመች መልኩ ማስተማር በተመለከተ ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚገኝ ጥናቱ አመላክቷል፡፡

የቃላት ማስተማሪያ መንገዶች መካከል ቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍች ማቅረብ ፤ቃላትን በአውድ ማቅረብ እና ቃላትን ከክሂሎች ጋር በማጣመር ከማቅረብ አንፃር ከፍተኛ በሆነ መልኩ እንደሚጠቀሙ በአንፃሩ የቃላት አብሮ ተሰላፊነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ ፣ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳት እና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ ፣የቃላት አካታች ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ማቅረብ እና ቃላትን ምንባብ በማዘጋጀት ከማቅረብ አንፃር ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚጠቀሙባቸው አጥኚው ተገንዝቧል፡፡ በተጨማሪ በቃላት ትምህርት መምህራን ተማሪዎችን የማሳተፍ ተግባሩ ዝቅተኛ መሆኑን እና ተማሪዎች ዝቅተኛ ተሳትፎ እንዳላቸው ጥናቱ አመላክቷል፡፡

## 5.3 አስተያየት

ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ጠቃሚ የሆኑ አስተያየቶችን መስጠት አስፈላጊ ነው፡ በዚህም አጥኚው በጥናቱ መሠረት ለቃላት ትምህርት አተገባበር ተግዳሮቶች መፍትሔ የሚሆኑ አስተያየቶች እንደሚከተለው ጠቅሷል ፡-

1.መምህራን ምንባብ በማዘጋጀት ቃላትን ማስተማር ፣ቃላትን ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ማቅረብ፣የቃላት አካታች ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ቃላትን ትምህርትን ማስተማር እና አብሮ ተሰላፊ ቃላትን መሰረት አድርጎ የቃላትን ትምህርት ከማስተማር አንፃር የመምህራን አጠቃቀም ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እነዚህ የማቅረቢያ ስልቶች ለዚህ የክፍል ደረጃ አስፈላጊና ተገቢ መሆናቸውን የተለያዩ ምሁራን ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ እነዚህን አስፈላጊና አጋዥ የሆኑ የማስተማሪያ መንገዶች መምህራን እንዲጠቀሟቸው ለመምህራን ግንዛቤና ስልጠናዎች ቢመቻች

2.የቃላት ማስተማሪያ መርሖች መምህራ ቃላትን ከማስተማራቸው በፊት ሊገነዘቧቸው የሚገቡ እንደሆኑ ምሁራን ገልጸዋል፡፡ መምህራን የቃላቱን ፍች ተጨባጭ ከማደረግ አንፃር በመርጃ መሳሪያ ሊደገፍ መቻሉ፣ለትምህርት የቀረበው ቃል ከተማሪው አፍ መፍቻ ቃላት ጋር ያለው የቅርፅ ተመሳስሎ ምን ያህል መሆኑ፣ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የተጣጣመ መሆኑ፣ከክፍለ ጊዜው ርዝማኔ ጋር ተመጥነው መቅረባቸው ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ፤ተማሪዎች የታላሚው ቃላት ችሎታ የሚያሳድጉት በቀረበላቸው አውድ ውስጥ የቃላትን ፍች

መተንበይ መቻልን ሲማሩ ነው፡፡ መምህራን ተማሪዎቻቸው የቃላት ችሎታቸውን በራሳቸው ጥረት እንዲያሳድጉና እንዲማሩ በዐውድ ውስጥ ቃላት እንዴት ፍችቻቸውን መተንበይ እንዳለባቸው ማለማመድ እንደሚገባ እንዲሁም ሁኔታዊ አቀራረብ ተከትሎ ማስተማር ተመራጭ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት በተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው እነዚህ የቃላት ማስተማሪያ መርሖች በተመለከተ ለመምህራን ግንዛቤያቸው ለማሳደግ አጫጭር ስልጠናዎችን ቢሰጥ

3. ለመምህራን የመምህሩ መምሪያ መጽሐፍ በእጥረት ምክንያት በእጃቸው ያለመኖሩ እና ለተማሪዎች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሐፍ በበቂ ሁኔታ ያለማዳረስ ለቃላት ትምህርት አቀራረብ እና አተገባበር ተግዳሮት መሆኑ በጥናቱ የተረጋገጠ ሲሆን ይህን የመምህሩ መምሪያ መሪ መጽሐፍ ለመምህራን በማዳረስ እና ለተማሪዎች በቂ የሆነ የመማሪያ መጽሐፍ በማቅረብ ችግሩን መቅረፍ ይገባል፡፡

4. መምህራን ከመማሪያ መጽሐፉ በተጨማሪ አጋዥ የሆኑ የማስተማሪያ ሰነዶችን በማዘጋጀት የቃላት ትምህርት ከማስተማር አንፃር ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ መምህራን ከመማሪያ መፅሐፍ በተጨማሪ አጋዥ የሆኑ የማስተማሪያ ሰነዶችን በማዘጋጀት የቃላት ትምህርት እንዲያስተምሩ ግንዛቤ ቢሰጥ

5 መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቃላትን ሲያስተምሩ ተማሪዎችን ዝቅተኛ በሆነ መልኩ እንደሚያሳትፉ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ለመምህራን በቃላት ትምህርት የተማሪዎች ተሳትፎ ወሳኝነት ግንዛቤ ቢሰጥ፤

## ዋቢ መጻህፍት


መስታወት ፀጋዬ። (2009) ። "በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳዳር በ2008 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ያሉት የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (ከ5ኛ-8ኛ ክፍል) የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍት የቃላት ትምህርት ይዘት አቀራረብ ግምገማ።"[ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት]። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ምንውየለት ደነቀው ።(2005)።"በአማራ ክልል በስራ ላይ ያሉት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሃፍት የቃላት ትምህርት የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ።" [ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት]።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

በልስቲ ጫኔ።(2013)።"የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ዝምድና ፍተሻ።" [ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት]።ጎንደር ዩኒቨርሲቲ።

ብሩክታዊት ተስፋዬ።(2001)። "በመቀሌ በሚገኙ ሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል የቃላት ትምህርት አተገባበር ፍተሻ።"[ያልታተመ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት]። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ባየ ይማም።(2000)። የአማርኛ ሰዋስው፣ (የተሻሻለው ሁለተኛው እትም)። አዲስ አበባ፣ ኢሌኒ ማ.ኃ.የተ.የግ.ማህበር።

ታሪኩ ፋንታዬ።(2004)።አማርኛ ሁሉለሁሉ።ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት።

አድኗል ደባልቄ ።(2013)። "አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ ሰባተኛ ክፍል የቃላት ትምህርት አተገባበር ፍተሻ (በሁለት ትምህርትቤቶች ተተኳሪነት)።"[ያልታተመ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት]። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ዘሪሁን አስፋው።(1996)። የስነ-ፅሁሑፍ መሰረታውያን። አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ያለው እንዳወቅ።(2009ዓ.ም)።የምርምር መሰረታዊ መርሆች አተገባበር። አዲስአበባ፣ተፈራ ስዩም ማተሚያ ቤት።

ደረበ ሙሉ፡፡(1999)፡፡ “በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ፡፡”[ያልታተመ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት]:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡(1990)፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡ አዲስአበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ጌታሁን አያና::(2011):: “በ9ኛእና10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት አቀራረብ ግምገማ፡፡”[ያልታተመ የሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት]:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

Alderson, J. C., Clapham, C., & Wall, D. (1995). Language test construction and evaluation. Cambridge University Press.

Cunnings-worth, A (1995). Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials. Oxford: Heineman International.

Eyrad, K. (2000). The Word Wall Approach; PromotingL2 Vocabulary learning. English Teaching Forum 38,3;1-11.

Harmer, J. (1991). The Practice of English Language Teaching. New York: Longman Group UK Limited.

Lewis, M. (1993). The Lexical Approach London: Commercial Color Press.

Macaro, E. (2001). Learning Strategies in Foreign and Second Language Classroom. London: Continuum.

McCarthy, M. (1990). Vocabulary. Oxford: Oxford University Press.

Maley, A (1990), The Word The Thing.Role . In.Hill.D.and Holden.S.(ed).Effective Teaching and Learning London ;Modern English publication 10-14.

Morgan,J and kinvlueri,M(1986). Vocabuiary and Reading.oxford.oup.

Nation, P. (2000). Learning Vocabuiary in Lexical Sets: Dangers and Guidelines. TESOL Journal. 9 (2): 6-10.

Nation, P. (2001). Learning Vocabuiary in Another Language. Cambridge: Cambridge University Press.

Nation, P. and Cody, J (1988). Vocabuiary and Reading in Carter R and McCarthy,M.(ed) Vocabulary and Language Teaching Newyork; longman group(UK0) Limited..

Richards, J. and Rodgers, T. (1999). Approaches and methods in language teaching (15th ed). USA, Cambridge University Press.

Richerds, J. (2001). Curriculum Development in Language Teaching Cambridge; Cambridge Publication.

Scholfield, P.J. (1997). Vocabulary Reference Works in Foreign Language.

Scrivener,J.(1998). Learning Teaching. Oxford: Macmillan Publishers Limited.

Summers,D.(1988).The Role of Dictionaries in Language Learning, In; Carter,R and McCarthy,M(ed), Vocabulary and language Teaching ,Newyork; Longman,111-113.

Taylo r,L,(1990). Teaching and Learning vocabulary, London: Prentice Hall.

Ur, P. (1996). A Course In Language Teaching Practice and Theory Cambridge: Cambridge university press.

Wallace,M.J.(1982). Teaching Vocabulary.London:Edward Arnold.

Wilkins, D.A. (1972). Linguistics in Language Teaching, London; Edward Arnold.

## አባሪዎች

### አባሪ 1፡- ለዘጠነኛ ክፍል መምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ

### አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

### የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

### የኢትዮጲያ ቋንቋዎች እና ሥነፅሑፍ ትምህርት ክፍል

### አማርኛ ማስተማር ሥነዘዴ መርሐ ግብር

### ድህረ ምረቃ ትምህርት

### በዘጠነኛ ክፍል መምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

**ማሳሰቢያ** ፡- ውድ **መምህራን** የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በጉራጌ ዞን በቡታጀራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠኛ ክፍል ተማሪዎች የቃላት ትምህርት አቀራረብ እና አተገባበር ምን እንደሚመስል መረጃ በመሰብሰብ ትንተና መስጠት ነው፡፡ መጠይቁ ሶስት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ክፍል መጠይቁን ስለሚሞሉት መምህራን አጠቃላይ መረጃ የሚገልፅ ነው፡፡ሁለተኛው ክፍል ስለቃላት ትምህርት አቀራረብ እና አተገባበር በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች መመሪያ ሲሆን በሶስተኛው ክፍል የመምህራን የግል አስተያየት የሚጠይቁ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ለምትሰጡት መልስ ታማኝ በመሆን ለጥናቱ ውጤት አስተማማኝነት የበኩላችሁን እንድታበረክቱ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡ በመጨረሻም ውድ መምህራን የትምህርት ጊዜያችሁን መሥዋዕት በማድረግ ላደረጋችሁልኝ ቀና ትብብር በቅድሚያ ምስጋናዬ ወደር የለውም፡፡

**ክፍል አንድ** ፡- የግል መረጃ መስጫ

የትምህርት ቤቱ ስም ----------------------------

የአገልግሎት ዘመን------------------------

ፆታ----------------------------

የሚያስተምርበት የክፍል ደረጃ -------------------

**ክፍል ሁለት፡- የጽሑፍ መጠይቅ መመሪያ**

ከዚህ በታች የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች የሚገልፁ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዱን ዐረተፍ ነገር በጥሞና አንብበሽ (ህ) የተጠቀሰውን የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ እና አተገባበር አስመልክቶ ከቀረቡ በጣም ከፍተኛ ፣ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ ከሚሉት አማራጭ መልሶች መካከል አንዱን ብቻ መርጠሽ(ህ) ከምርጫው ፊት ለፊት በሚገኘው ሳጥን ውስጥ የ "√" ምልክት በማድረግ መልሽ(ስ)፡፡

**የመመዘኛዎች መግለጫ፡-** 5 /በጣም ከፍተኛ/ 4 /ከፍተኛ/ 3 /መካከለኛ/ 2 /ዝቅተኛ/

1 /በጣም ዝቅተኛ/

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቃላትን ትምህርት በክፍል ውስጥ አቀርባለሁ | | | | | |
| 2 | ቃላትን በአውድ አስተምራለሁ | | | | | |
| 3 | ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካይነት ከማቅረብ አንፃር | | | | | |
| | 3.1 ቃላትን በተመሣሣይ እና በተቃራኒ ፍቻቸው አቀርባለሁ | | | | | |
| | 3.2 የቃላት የቃላትን አካታችና ተከታች መሰረት አድርጌ ቃላትን ትምህረት አቀርባለሁ | | | | | |
| | 3.3 አብሮ ተሰላፊ ቃላትን መሰረት አድርጌ ቃላትን አስተምራለሁ | | | | | |
| 4 | የቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጌ አቀርባለሁ | | | | | |
| 5 | ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፌ አቀርባለሁ | | | | | |
| 6 | ቃላትን ቋንቋ ከክሂሎች ጋር አቀናጅቼ አስተመራለሁ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | ምንባብ በማዘጋጀት ቃላትን አስተምራለሁ | | | | | |
| 8 | ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላት አስተምራለሁ | | | | | |
| 9 | ቃላትን ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት አቀርባለሁ | | | | | |
| 10 | ለቃላት ትምህርት መማርያ መፅሐፉን እጠቀማለሁ | | | | | |
| 11 | ለቃላት ትምህርት ከመማሪያ መፅሐፉን በተጨማሪ አጋዥ የሆኑ የማስተማሪያ ሰነዶችን በማዘጋጀት የቃላት ትምህርት አስተመራለሁ | | | | | |
| 13 | መርሃ ትምህርቱ ለቃላት ትምህርት ለማስተማር የሚረዱ ዘዴዎችን ያሳያል፡፡ | | | | | |

**ክፍል ሶስት**

ከዚህ በታች በቀረቡ ጥያቄዎች ክፍት ቦታዎች ላይ ተገቢ መልስ ስጡ፡፡

1. በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የቃላት ትምህርት እንዴት አድርገው ክፍል ውስጥ ይተገብሩታል? ምን ምን ዘዴዎችን ይጠቀማሉ? ------------

2. ለቃላት ትምህርት የመምህሩ መምሪያ ከአቀራረብ እና ከአተገባበር አንፃር ምን ያህል አጋዥ ነው ብለው ያስባሉ?------------------

3. የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች ከሚባሉት የትኛውን መንገድ ይበልጥ ይጠቀማሉ? ለምን? --------------------------------------

4. የቃላት ትምህርት ሲያስተምሩ ከተማሪዎች ምን አይነት ተግዳሮቶች ያጋጥሞታል? የወሰዱት መፍትሔስ ምንድ ነው?----------------

5. የቃላት ትምህርት አቀራረብ እና አተገባበር በተመለከተ ስልጠናዎችን ወስደው ያውቃሉ? መልሶ “አዎ” ከሆነ ምን እገዛ አደረገሎት?

## አባሪ 2 ፡- ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ
## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነፅሑፍ ትምህርት ክፍል

## አማርኛ ማስተማር ሥነዘዴ መርሐ ግብር

## ድህረ ምረቃ ትምህርት

## በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

**ማሳሰቢያ ፡- ውድ ተማሪዎች** የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በጉራጌ ዞን በቡታጀራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ያደረገ የቃላት ትምህርት አቀራረብ እና አተገባበር ምን እንደሚመስል መረጃ በመሰብሰብ ትንተና መስጠት ነው፡፡ መጠይቁ ሶስት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ክፍል መጠይቁን ስለሚሞሉት ተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ የሚገልፅ ነው፡፡ሁለተኛው ክፍል ስለቃላት ትምህርት አቀራረብ እና አተገባበር በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች መመሪያ ሲሆን በሶስተኛው ክፍል በተማሪዎች የግል አስተያት የሚጠይቁ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ለምትሰጡት መልስ ታማኝ በመሆን ለጥናቱ ውጤት አስተማማኝነት የበኩላችሁን እንድታበረክቱ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡ በመጨረሻም ውድ ተማሪዎቻችን የትምህርት ጊዜያችሁን መሥዋዕት በማድረግ ላደረጋችሁልኝ ቀና ትብብር በቅድሚያ ምስጋናዬ ወደር የለውም፡፡

ማሳሰብያ፡- 1. መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

2.በሚሰበሰበው መረጃ ውጤቱ ላይ ተፅኖ እንዳያሳድር መጠይቁን ብቻዎን ይሙሉ

**<u>ክፍል አንድ ፡-</u>** የግል መረጃ መስጫ

የትምህርት ቤቱ ስም------------------------------ የክፍል ደረጃ-----------------

እድሜ----------------------- ፆታ ----------------------------

***ክፍል ሁለት፡- የጽሑፍ መጠይቅ መመሪያ፡-*** ከዚህ በታች የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች የሚገልፁ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዱን ዐረተፍ ነገር በጥሞና አንብበሽ (ህ)የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ እና አተገባበር አስመልክቶ ከቀረቡ በጣም ከፍተኛ ፣ ከፍተኛ ፣ መካከለኛ ፣ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ ከሚሉት አማራጭ መልሶች መካከል አንዱን ብቻ መርጠሽ(ህ) ከምርጫው ፊት ለፊት በሚገኘው ሳጥን ውስጥ የ "√" ምልክት በማድረግ መልሽ(ስ)፡፡

***የመመዘኛዎችመግለጫ፡-*** 5/በጣም ከፍተኛ/ 4 /ከፍተኛ/ 3 /መካከለኛ/2 /ዝቅተኛ/ 1 /በጣም ዝቅተኛ/

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቃላትን ትምህርት በክፍል ውስጥ ትማራላችሁ | | | | | |
| 2 | የቃላትን ትምህርት በአውዳዊ አገባብ ያስተምሯችኃል | | | | | |
| 3 | ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካይነት ከማቅረብ አንፃር | | | | | |
| | 3.1 የቃላትን ተመሣሣይ እና ተቃራኒ ፍቻቸው ትማራላችሁ | | | | | |
| | 3.2 የቃላት የቃላትን አካታችና ተከታች መሰረት አድርጎ ቃላትን ትምህርት መምህሩ ያስተምሯችኃል | | | | | |
| | 3.3 አብሮ ተሰላፊ ቃላትን መሰረት አድርጎ የቃላትን ትምህርት ትማራላቹ | | | | | |
| 4 | የቃላትን ትምህርት በእርባታና በምስረታ ስርዓት መሰረት አድርገው ያስተምሯችኃል | | | | | |
| 5 | የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ያቀርቡሏችኃል | | | | | |
| 6 | ቃላትን ከክሂሎች ጋር አቀናጅተው ያስተምሯችኃል | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | መምህራን ምንባብ በማዘጋጀት ቃላትን ያስተምሯችኃል | | | | | |
| 8 | ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላት ትማራላችሁ | | | | | |
| 9 | ቃላትን ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ያቀርቡላችኃል | | | | | |
| 10 | የቃላትን ፍቺ በተለያዩ ገለፃዎች መምህሩ ያቀርቡላችኃል | | | | | |
| | የቃላት ትምህርት መማሪያ መፅሐፉን ተጠቅሞ ያስተምሯችኋል | | | | | |
| 12 | መምህራን ለቃላትን ትምህርት ከመማሪያ መፅሐፉ በተጨማሪ አጋዥ የሆኑ የማስተማሪያ ሰነዶችን በማዘጋጀት ያቀርቡላችኃል | | | | | |
| 13 | የቃላት ትምህርትን ስትማሩ ጥያቄዎችን በመመለስ ፣በመጠየቅ እና ክፍል ውስጥ በሚነሱ ትምህርታዊ ጉዳዮች ላይ ትሳተፋላችሁ | | | | | |

**ክፍል ሶስት ፡-ከዚህ በታች በቀረቡ ጥያቄዎች ክፍት ቦታዎች ላይ ተገቢ መልስ ስጡ።**

1. ቃላትን ስትማሩ የሚያጋጥሟችሁ ችግሮች ምን ምን ናቸው?------------------------------

2.ተጨማሪ ስለ ቃላት ትምህርት አስተያየት ካለ--------------------------

**አባሪ 3:- የቃላት ትምህርት ክንውን መከታተያ ቅፅ**

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የቋንቋዎች ጥናት ተቋም**

**የኢትዮጲያ ቋንቋዎች እና ሥነፅሑፍ ትምህርት ክፍል**

**አማርኛ ማስተማር ሥነዘዴ መርሐ ግብር**

**ድህረ ምረቃ ትምህርት**

**በክፍል ውስጥ የቃላት ትምህርት ክንውን መከታተያ ቅፅ**

ይህ ጥናት በጉራጌ ዞን በቡታጀራ ከተማ በበህር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ያደረገ የቃላት ትምህርት አቀራረብ እና አተገባበር ምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ የሚደረግ የክፍል ውስጥ ምልከታ ቅፅ ነው፡፡

የክፍል ምልከታ ቅፅ አጠቃላይ መግለጫ፡-

የትምህርት ቤቱ ስም ------------------

ምልከታ የተካሄደበት የክፍል ደረጃ ------------------

ምልከታ የተደረገበት ቀን--------------ወር----------ዓመተ ምህረት-----

ምልከታ የተደረገበት ክ/ጊዜ---------------------------

ምልከታ የተደረገበት ሰዓት----------------------------

ቀጥሎ በሰንጠረዥ ለቀረቡ ዝርዝር የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅፅ መልስ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ አምስት አማራጮች በመጠቀም ምልከታውን አድረጓል፡፡

1.በጣም ዝቅተኛ 2.ዝቅተኛ 3.መካከለኛ 4.ከፍተኛ 5. በጣም ከፍተኛ

| ተ.ቁ | የምልከታ መስፈርቶች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቃላት ትምህርት ማስተማርያ መርሖች በተመለከተ | | | | | |
| | 1.1ዓላማን ስለመያዝ | | | | | |
| | 1.2 የቀረቡ የቃላት ትምህርት ይዘት ከክፍለ ጊዜው እና ከተማሪዎች ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ | | | | | |
| | 1.3 የቃላትን ትምህርት ለትውስታ በሚመች መልኩ ስለማስተማሩ | | | | | |
| | 1.4ሁኔታዊ አቀራረብ ስለመከተሉ | | | | | |
| | 1.5ቃላትን ለትንበያ በሚመች መልኩ ስለማቅረቡ | | | | | |
| | 1.6ቃላትን በተመሳሳይ ባህሪያቸው አቧድኖ ስለማቅረቡ | | | | | |
| 2 | መምህሩ ተማሪዎችን አቀማመጥ መቼነት በተመለከተ ስለማረጋገጡ | | | | | |
| 3 | የቃላትን ትምህርት በአውዳዊ አገባብ መሰረት አድርጎ ከማስተማር አንፃር | | | | | |
| 4 | ቃላትን በፍቺ ተዛምዷቸው አማካይነት አድረገው ከማስተማር አንፃር | | | | | |
| | 4.1 የቃላትን ተመሣሣይ እና ተቃራኒ ፍቻቸው ስለመማራቸው | | | | | |
| | 4.2 የቃላትን አካታችና ተከታች ግንኙነት መሰረት አድርጎ ቃላትን ትምህርት መምህሩ ስለማቅረቡ | | | | | |
| | 4.3 አብሮ ተሰላፊ ቃላትን መሰረት አድርጎ የቃላትን ትምህርት ስለመማራቸው | | | | | |
| 5 | የቃላትን ትምህርት በእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ከማስተማር አንፃር | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | የቃላትን ትምህርት መዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማስተማር አንፃር | | | | | |
| 7 | ቃላትን ቋንቋ ከክሂሎች ጋር አቀናጅተው ከማስተማር አንፃር | | | | | |
| 8 | መምህራን ምንባብ በማዘጋጀት ቃላትን ከማስተማር አንፃር | | | | | |
| 9 | ግልፅ የሆነ መመሪያ በማቅረብ ቃላት ከማስተማር አንፃር | | | | | |
| 10 | ቃላትን ሀረጎችን ለመረዳትና ለማፍለቅ በሚያስችል ስልት ስለመቅረቡ | | | | | |
| 11 | መምህራን የቃላት ትምህርትን መማሪያ መፅሐፉን ተጠቅመው ከማስተማር አንፃር | | | | | |
| 12 | መምህሩ ከመማሪያ መፅሐፉ በተጨማሪ አጋዥ የሆኑ የማስተማሪያ ሰነዶችን በማዘጋጀት የቃላት ትምህርት ከማስተማር አንፃር | | | | | |
| 13 | በቃላት ትምህርት የተማሪዎች ተሳትፎ በተመለከተ | | | | | |
| 14 | መምህሩ ተማሪዎችን በቃላት ትምህርት የማሳተፍ ተግባሩ | | | | | |